አጽዋማትና በዓላት ከ፲፱፻፺፯ - ፪ሺ፲

፲፱፻፺፰ ወንጌላዊው ማርቆስ ዘ.መ እሑድ አበቅቴ ፩ መጥቅዕ ፳፱ የዕ. ተውሳክ ፯ ጾ.ነነዌ የካ ፮ ዐ.ጾም የካ ፳ ደ.ዘይት መጋ ፲፯ ሆሳዕና ሚያ ፳ ስቅለት ሚያ ፲፫ ትንሣኤ ሚያ ፲፭ ር.ካ ግን. ፱ ዕር ገት ግን ፳፱ ጸራቅሊጦስ ሰኔ ፱ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፯

፲፱፻፺፱ ወንጌላዊው ሉቃስ ዘ.መ ሰኞ አበቅቴ ፲፪ መጥቅዕ ፲፰ የዕ. ተውሳክ ፫ ጾ.ነነዌ ጥር ፳፩ ዐ.ጾም የካ ፭ ደ.ዘይት መጋ ፪ ሆሣዕና መጋ ፳፫ ስቅለት መጋ ፳፰ ትንሣኤ መጋ ፴ ር.ካ ሚያ ፳፱ ዕርገት ግን ፱ ጸራቅሊጦስ ግን ፲፱ ጾ.ድኅነት ግን ፳፪

፪ሺ. ወንጌላዊው ዮሐንስ ዘ.መ ረቡዕ አበቅቴ ፳፫ መጥቅዕ ፯ የዕ. ተውሳክ ፫ ጾ.ነነዌ የካ ፲ ዐ.ጾም የካ ፳፱ ደ.ዘይት መጋ ፳፩ ሆሣዕና ሚያ ፲፪ ስቅለት ሚያ ፲፯ ትንሣኤ ሚያ ፲፱ ር.ካ ግን ፲፫ ዕርገት ግን ፳፰ ጸራቅሊጦስ ሰኔ ፰ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፲፩

፪ሺ፩ ወንጌላዊው ማቴዎስ ዘ.መ ሐሙስ አበቅቴ ፬ መጥቅዕ ፳፯ የዕ. ተውሳክ ፯ ጾ.ነነዌ የካ ፭ ዐ.ጾም የካ ፲፯ ደ.ዘይት መጋ ፲፰ ሆሣዕና ሚያ ፬ ስቅለት ሚያ ፱ ትንሣኤ ሚያ ፲፩ ር.ካ ግን ፭ ዕርገት ግን ፳ ጸራቅሊጦስ ግን ፳፮ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፫


፪ሺ፪ ወንጌላዊው ማርቆስ ዘ.መ ዓርብ አበቅቴ ፲፭ መጥቅዕ ፲፭ የዕ. ተውሳክ ፭ ጾ.ነነዌ ጥር ፲፯ ዐ.ጾም የካ ፩ ደ.ዘይት የካ ፳፫ ሆሣዕና መጋ ፲፱ ስቅለት መጋ ፳፬ ትንሣኤ መጋ ፳፯ ር.ካ ሚያ ፳ ዕርገት ግን ፭ ጸራቅሊጦስ ግን ፲፭ ጾ.ድኅነት ግን ፲፰

፪ሺ፫ ወንጌላዊው ሉቃስ ዘ.መ ቅዳሜ አበቅቴ ፳፯ መጥቅዕ ፬ የዕ. ተውሳክ ፫ ጾ.ነነዌ የካ ፯ ዐ.ጾም የካ ፳፩ ደ.ዘይት መጋ ፳፫ ሆሣዕና ሚያ ፱ ስቅለት ሚያ ፲፬ ትንሣኤ ሚያ ፲፮ ር.ካ ግን ፲ ዕርገት ግን ፳፭ ጸራቅሊጦስ ሰኔ ፭ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፰

፪ሺ፬ ወንጌላዊው ዮሐንስ ዘ.መ ሰኞ አበቅቴ ፲ መጥቅዕ ፳፫ የዕ. ተውሳክ ፭ ጾ.ነነዌ ጥር ፳፰ ዐ.ጾም የካ ፲፪ ደ.ዘይት መጋ ፲፭ ሆሣዕና መጋ ፴ ስቅለት ሚያ ፭ ትንሣኤ ሚያ ፯ ር.ካ ግን ፩ ዕርገት ግን ፲፯ ጸራቅሊጦስ ግን ፳፪ ጾ.ድኅነት ግን ፳፱

ሠርክ ኅብስት

በአባ ገብረ መድኅን ከበደ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
እምነት የተዘጋጀ

1998 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

- መቅድም 3
- መሠረታዊ አቀማመጥ 5
- የቤተ ክርስቲያን ሠርከ ጎብስት 10
- አሮጌውን ተውት አዲሱን ልበሱት 12
- ሥልጣን ሰላምና ነፃነት የለውም 16
- የእግዚአብሔር ቃል አያልፍም 23
- ዘየአሲ ተወካፊ (የሚሰጥ ይቀበላል) 25
- የገበሬ መልካም አስተዳደር 30
- ግብረ ጠልነት ምንደኛነት ነው 34
- እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን 36
- ሥልጣን በሐዲስ ኪዳን ዘመን አሮጌ ሥርዓት ነው 38
- የቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ሥርዓት 40
- ‹‹ጸጋ በዲበ ጸጋ ተውህበ ለነ›› (በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል) 43
- የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም 46
- ሲኖዶስ የገዳማት አካል ነው 54

መቅድም

ሠርከ ጎብስት

ሰርክ ጎብስት ማለት ውሉ የሚቀመስ የመናንያን ምግብ ማለት ብቻ ሳይ ሆን በዓይነት በዓይነት እየተዘጋጀ የሚቀርብ ለሰውነት የሚስማማ ተመጣጣኝ የዘውትር ቁርስ፣ ምሳ፣ ራት ማለት ነው። የቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች አንድነትም በዓለማዊ ሥርዓት ወይም በኂላቀር ሥልጣን የማይለካ በተሟላ የሥርዓተ ማኅበር ሠርክ ጎብስት ተጠብቆ የሚኖር ቤተ ክርስቲያን ከጊዜ ወደ ጊዜ የምታድግበት ማለት ነው።

የዓለምና የቤተ ክርስቲያን አቀማመጥ የተለያየ ነው፤ ዓለም ከራሱ ብቻ ይነሣል፤ ራሱን የሚያስገዛበት ባለቤት የለውምና መጨረሻው ጥፋት ነው። በሕያውነቱ ሕይወትን ለሚሰጥ ለእግዚአብሔር መገዛት ግን ዋስትና ባለቤት ስላለው እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር ሕይወትና ሰላም ነው።

የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲጠነክርበትና ቤተ ክርስቲያን አንድታድግበት ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን የሚለግሱት ገንዘብ የቤተ ክርስቲያን ሠርከ ጎብስት (የዕለት ምግብ) ይባላል፤ ሠርከ ጎብስት የቤተ ክርስቲያን አንድነት መገንቢያ ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ተመልሶ የዓለም ይዞታ እንዲሆን አይፈቀድም።

ባለቤት ገበሬ ወይም ነጋዴ በቤቱ ከሠርከ ጎብስት ከዕለት ምግብ በላይ ሌላ ነገር እንደማያስፈልገው የቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በሠርከ ጎብስት ብቻ ተወስነው እንዲሠሩበት፤ ለምን ደኖው ሠራተኛ ደመወዝ እንዲከፍሉበት እንጂ ከባለቤትነት ውጭ ከምንደኛው ጋር ደመወዝ እየተቀበሉ በደመወዝ ስም የቤተ ክርስቲያንን ሠርከ ጎብስት ወደ ውጭ ሊያወጡትና የግል ቤት ሊሠሩበት አልተፈቀደም። ሚመተ ጵጵስና ሰባ ለቤትነት ነው ለደመወዝ አይደለም። የቅዱስ ሲኖዶስ ክብርና ሞገስ ሐዋርያዊ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ባለቤትነት ነው እንጂ ደመወዝ አይደለም፤ ሆኖም ከደመወዝ ይልቅ የባለቤትነት የሠርከ ጎብስት ወጪ ይበልጣል።

የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ እንደፈለጉ በማድረግ የመንግሥተ እግዚአብሔርን ሥራ ማከናወን አይቻልም፤ የባለቤትነት ብልጽግና ከደመወዝ አይደለም ከሥራ ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ያለ ደመወዝ በባለቤትነት ሊሠራበት እያደገ ሊመጣ ይችላል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አድማስ እየ ሰፋ መጥቷል ለማለት የሚያስችለው የቤተ ክርስቲያኗ ሠርክ ጎብስት እንዲበ ዛና አንድነቷ እንዲጠነክር ንብረቷን የሚቈጣጠሩ በርካታ ባለቤቶች ሲኖሩላት ነው፤ ቤተ ክርስቲያኗና የቤተ ክርስቲያኗ ርእስ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ክብር ነፃነት የሚኖረው በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ጊዜ ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር የሠራው ሥራ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ከሥልጣን ነፃ የሆነ ነበር። የተሾመበትን ሥራ የባሕርይ አባቱን ፈቃድ ብቻ ሊፈጽም ሊቀ ካህናት ተብሎ ተሾመ፤ የተሾመም እንደ ሥርዓቱ ይሾማ ልና ጌታችን ሹሞ የላካቸው ደቀ መዛሙርት ከሀገታቸው ፈጣን የተልዕኮ ሹመት ሆኖላቸው ከዓለማዊ ጥቅማ ጥቅም ነፃ ሆነው በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ቤተ ክርስቲያንን መሥርተው አደራጅተዋል።

አሁንም በሐዋርያት የተደራጀችው ቤተ ክርስቲያን በዓለማዊ ሥርዓት ትፍረስ፣ ዓለም ይዋጣት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ይቅር አይባልምና በግል ሥልጣን ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር ለመንፈሳዊ አቋም እንቅፋት መሆኑን የተገነዘቡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሐዋርያትን ሥር ዓተ ማኅበር አስተዳደር ይጠቀሙበታል፤ ለወዳጅ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት ዕርዳታ ከሠርክ ጎብስታቸው (ከሥርዓተ ማኅበራቸው) የተረፈ ነው። ቤተ ክር ስቲያን ደመወዝተኛ የዓለም ጎጆ ወጪ አይደለችምና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች ያለ ደመወዝ በተሟላ ሠርክ ጎብስታቸው ተደ ራጅተው የሐዋርያትን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር መሪዎች ቢሆኑ የገዳማ ትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን አገልግሎትን ማሟላት እንደሚቻል ይታመናል።

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ሰሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳ ችሁ ተጠንቀቁ» የተባለባቸው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ያለ ደመወዝ በባለቤ ትነት ሠርክ ጎብስት ተወስነው የመማርና ማስተማር፣ የልማት የሕክምና አገ ልግሎትና የቴክኒክ መሪዎች ሆነው የሰማይም የምድርም ክብራቸው የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን ንብረት እያስጠበቁ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሥሪቷ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ባለቤትነት እንዲኖራት ሊያስፈልግ ነው ዕድገት ሊኖራት የሚችለው።

የቤት ባለቤት

መሠረታዊ አቀማመጥ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

የቤት ባለቤት ማለት ከራሱ ተግባርና ኃላፊነት በምንደኝነት ተግባር ወደኋላ የማይርቅ ሥራውን ፈጻሚና አስፈጻሚ ማለት ነው፤ ስለራሱ ቤትና ክብር በምንደኝነት ያልተከፈለ አምነት አለው። ለሐዋርያነት ከእግዚአብሔር የተሾመ የቤተ ክርስቲያን ባለቤት ራሱ ብቻ የሚራመድበት የራሱ እምነት ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ታማ ኝነትም አለው፤ ታማኝነት ተሰጥቶታል፣ ከሚሠራ የሚያሠራ ባለ ቤት ይበልጣልና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳኝነት ሥራ ውን በፍቅር ፈጽሞታል፤ ባለቤቶች ሁነው ቤተ ክርስቲያንን እን ዲጠብቁ ሐዋርያትን ሹሚል።

እንዲህም አለ *«ዘረ ስኔ ነኝ፣ በስኔ የሚገዝ ቢኖር ይድናል፣ ይገባልም፣ ይመ ጣልም፤ በሠማሪያም ያገኛል፤ ሲባዙ ሲሰርቁና ሲያርድ ሲያጠፋም ስንጂ ስሰ ሲሳ ስይበሰጣም፤ ስኔ ሕያሠት ስንዲሆንላችው ስንዲበዛላችውም መጣሁ። መልካም ስረኛ ስኔ ነኝ መልካም ስረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል፤ ስረኛ ያልሆነው በጎ ቹም የስርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኵሳ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ተቶ ይሸሻል፤ ተኵሳም ይነጥቃቸዋል፤ በጎቹንም ይበትናቸዋል፤ ሞያተኛ ስለሆነ ስለበጎቹ ስሰ ማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል።»*

መልካም ስረኛ ስኔ ነኝ ስብም ስንደሚያውቁኝ ስኔም ስብን ስንደማውቀው የራሴን በጎች ስውቃስሁ፣ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስስበጎች ስኖራ ስሁ፤ ከዚህ በረተ ያልሆኑ ሌሱች በጎች ስስኙ፤ ስነርሱን ደገሞ ባመጣ ይገባኛል፤ ድምጼንም ይሰማሱ ስንድ መንጋ ይሆናሱ ስረኛቸውም ስንድ፤ (ዮሐ.10፡6-16)

ከጌታው ጋር የቈየ ጌታውን ያውቃልና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን "እኔ ማን ነኝ ሲለው ቅዱስ ጴጥሮስ

ሲመልስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለው፤ ‹‹ኢየሱስም መልሶ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም አል ገለጸልህምና ብፁዕ ነህ አንተ ጴጥሮስ ነህ ዓለት ነህ በዚችህም አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሐነም ደጆች አይች ሉአትም፤ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻ እሰጥሻለሁ፤ በም ድር ያሰርከው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድር የፈታኸው በሰ ማያት የተፈታ ይሆናል›› በማለት የሰማዩንም የምድሩንም ሥል ጣን ሰጠው፤ (ማቴ.16፥13-19)

አሁንም ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን ‹‹ፈጸመኪ ለጣግዕየ›› በጎቼን ምእመናንን ጠብቅ ‹‹ፈጸመኪ መሐለስየ›› በጎቼን ሕፃናትን ጠብቅ ብሎታል፤ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጴጥሮስን የምታክል ታዋቂ ትንሽ መንደር ሆና ነው የተመሠረተችው።

መሥዋዕትነቱ ተፈጽሞ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣና ሐዋርያትን ሹሞ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ብሎ ከዐረገ በኋላ ቤተ ክርስቲያን በተሾሙት ሐዋርያት ላይ ተመሠረተች፤ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ አደረ፤ ቤተ ክር ስቲያን ታነጸች፤ ምእመናን በዚህ ሕንጻ ውስጥ እንዲያድጉና የጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆኑ የክርስትና እምነት ከአይሁዳውያን ተጀምሮ የመላው ዓለም ሕዝብ እምነት እስኪሆን ድረስ ስለ መን ግሥተ ሰማያት እግዚአብሔር የሚናገረው የምሥራች ቃል በኢየ ሩሳሌም በይሁዳ አገርና በሰማርያ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ተሰበከ።

በመንፈሳዊ ታሪክ እንደምናውቀውና አውቀንም እንደምናም ንበት በእስራኤል አገር በጎች እረኞቸውን ይለምዱታል ብለውም ይወዱታል፤ እረኞቸው በፊት ለፊታቸው ሲሄድ ድምፁን እየሰሙ ይከተሉታል፤ ሣርና ውሃ ወዳለበት ይመራቸዋል።

መልካም እረኛ ታማኝ ነውና ቤተ ክርስቲያን መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስን ታምናና ተከትላ ምእመናን ድምጿን ትምህርቷን የሚሰሙበትና የሚበዙበት አርአያነት ያለው ሥርዓትና መልካም መንፈሳዊ አስተዳደር እረኛነት እንዲኖራትና የመንግሥተ እግዚአ ብሔር ሥራ በእርሷ እንዲካተት ሆና ነው የተመሠረተችው።

ቤተ ክርስቲያን አደራነትን ጠብቃ ለሥራ የምትነሣ የምሥ ራቹን ቃል በሰው ዘንድ እያሳመነች ሕዝብን የምታበዛ የመንግ ሥተ እግዚአብሔርን ወራሽነት የምትጠባበቅ መርሕ ናት። አተ ርፍ ባይ አጉዳይ ዓለማዊ ነጋዴ ያልሆነች የዳግም ልደት ዘለዓለ ማዊ ሕይወትን የምታድል ሆና እንጂ ከራሱ ትምክህት ከሚነሣ ራሱን ከማያድን የእግዚአብሔርን አደራነት ከማይጠብቅ ዘላቂ ሕይወትና ሰላም ከሌለው ዓለም ጋር አንድነት እንዲኖራት ሳይ ሆን በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር መልካም አርአያነቷ ዓለምን የም ታሳምንና በዓለማዊነት ወደኋላ የማትል ሆና ነው የተመሠ ረተችው።

የታማኝነት ሥራ ነፃነት ያለው ነው፤ የነፃነት ሂደትም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር የሚዳኝ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ነው፤ ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ሥራዋ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተጠበቀ የሚያድግ ሆኖ የሥልጣን ነቀፌታና ችግር ሳይ ኖርባት በዙሪያዋ መንፈሳዊ ክብርና ሞገስ ሰፍኖ እንዲኖር ሆና ነው የተመሠረተችው።

ቤተ ክርስቲያን ትርጉሟ በየጊዜው ጊዜውን ለመዋጀት የቆ መች ከፀጋው በታች እንጂ ከሕግ በታች ያልሆነች፣ ሕግን የም ትቈጣጠር እንጂ ሕግ የማይቈጣጠራት ዓለም (ኃጢአት) የማይ ገዛት፣ በቁመተ ሥጋና በቁመተ ነፍስ ብቻ የታመነች፣ ከቁመተ

ሥጋ በላይ ምንም ዓይነት ጥቅም የማትፈልግ፣ አንድነቷን የሚ
ያጠነክር፣ ቀኖናዋን የሚጠብቅ፣ አገልግሎቷን የሚያስከብር የሥ
ርዓተ ማኅበር አስተዳደር እንዲመራት ነው የተመሠረተችው፤
አንድነት የማይስማማውና አንድነትን የሚያፈርስ ሥልጣን የሚ
መራት ሆና የተመሠረተች አይደለችም፤ ቤተ ክርስቲያን ወርዷ
ቁመቷ ጠቅላላ አካሏ አንድነቷ ነው፤ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳ
ደርም ሥሪቷ ነው።

ክፍል ሁለት

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ከዚህ ዓለም ውስብስብ ነገር ነፃ
ሆኖና ራሱን ችሎ ከክርስትና እምነት ከዳግም ልደት ይነሣል፤
ከሚጠፋ ዓለም ጋር እየተዛመደ መንፈሳዊ ሕይወቱን አንድነቱንና
ነፃነቱን ወደኋላ አያስቀርም።

ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ አደራነት የክርስቶስ ፍቅር ብቻ ነው፤
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ‹‹*በፍቀሬ ኮረ*
ስኔ የሰባቴን ተስዛዝ ስንደጠበቀሁ በፍቀረም ስንደምናር ተስዛዚን ብተጠብቁ
በፍቀሬ ተኖራብችሁ፤ ደስታዩም በስናንተ ስንዲሆን ደስታችሁም ስንዲፈጸም
ነግሬያችኋስሁ፤ ስኔ ስንደመደድኋችሁ ስርስ በርዛችሁ ተዋደዱ ዘንድ ተስዛዚ
*ደህች ናት›› እንዳላቸው የቤተ ክርስቲያን ሥራ የጋራ ሕይወት ነው፤
(ዮሐ.15፥10-12)

ሥልጣን ከልማድ የተገኘ ነው፤ የሥራ አንድነት ግን በክ
ርስቶስ ፍቅር ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር
አቋም የሚገነባ ነው፤ ክሊቀ ካህናት ክርስቶስ ለሐዋርያት የተሰጠ
ሥልጣን ተልእኮ ነው፤ በሐዋርያዊነት ሥርዓት ጊዜ የሥልጣን
ጭቅጭቅና መለያየት አይኖርም፤ የሐዋርያዊነት ነፃ አገልግሎት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ከዚህ ዓለም ነፃ አድርጎ
በፍቅሩ የመሠረተው የደኅንነት ዓላማ ነው፤ ለመዳንና ሌላውንም
ለማስተማር ከጌታችን እንጂ ከዓለም የሚፈለግ ነገር የለም። የሥጋ
ጥቅም ከዓለም ስለሚገኝም ዓለምን ወደ እግዚአብሔር መንግ
ሥት መጋበዝ ትልቁ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ሆነ።

ቤተ ክርስቲያን ዓለምን መቶ እጥፍ የእግዚአብሔር ገንዘብ
ለማድረግ የተልእኮ ሥልጣን ተሰጥቷታል፤ የዓለምን ሒሳር የናቀ
‹‹*ደረክብ ምስተ ምክብሲተ*›› በናቀው ዓለማዊ ክብር ፈንታ መቶ እጥፍ
ያገኛል፤ ለምሳሌ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ባለቤቶች ሁነው በሥ
ርዓተ ማኅበር አስተዳደር ቤተ ክርስቲያንን ቢመሩ ደመወዝ ባይ
ቀበሉና የግል ቤት ባይሠሩ ‹‹*ምስተ ምክብሲተ ደረክቡ*›› ሠርክ ጎብኝ
ታቸው መቶ እጥፍ ይሆናል፤ ክብራቸው ከዳር እስከ ዳር ከጽንፍ
እስከ ጽንፍ ይታወቃል፤ (ማር.10፥29፣3) ዓለምን ያልናቀ ፍቅረ
ንዋይ (የገንዘብ ፍቅር) (ምእተ ምክብኢተ) ዓለም መቶ እጥፍ የቤተ
ክርስቲያን ገንዘብ እየሆነ አንዳይመጣ ይከለክላል።

ዓለምን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊለውጥ የሚችል
የቤተ ክርስቲያን ባለቤትነት ነው፤ ባለቤትነት ሊለካ የሚችለውም
ያለ ደመወዝ ነው፤ ባለቤትነት በሁለት ልብ ያልተከፈለ ነው፤ ቤተ
ክርስቲያን ባለቤቶቿ ጥቅም ይዘው ሳይወጡ የሚያድሩባት የመ
ኖሪያ ቤት ናት፤ መዋያ ብቻ እንዳትሆን ገንዘቧ የዓለም ቤተሰብ
መመጻደቂያ ሆኖ ባዶ እንዳትቀር ሠርክ ጎብኝቷን እንዲያሳድግና
አንድነቷን እንዲጠብቅ በባለቤትነት ተግባር የተጠበቀ መሆን
እንዳለበት ነው የሚታመነው።

የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ከሥርዓተ ማኅበር ውጭ በዓለማ
ዊነት ቢይዙት የእግዚአብሔር ጸጋ ሳያበዛ የዓለም ይዞታ ሆኖ
ይቀራል፤ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት አይሠራም፤ ቤተ ክርስቲያን

ደመወዝ የማይበላ ባለቤት እስክሌላት ድረስ የስም ሀብት ቢኖ ራትም ባዶ ናት፤ ገንዘቧ የተበዘበዘና የተዘረፈ ይሆንባታል፤ መን ፈሳዊ ሕይወቷ እያዘነ እየተለያየና እየተበላሸ ይኖራል፤ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ሰብሳቢና ጠባቂ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሥ ርዓተ ማኅበር አስተዳደር መሆኑ መታወቅ አለበት፤ ዓለምን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ክልል የሚጋብዝ የቅዱስ ሲኖዶስ አባ ላት አባቶች በቤተ ክርስቲያን ሠርክ ጎብስት ተወስነው በሥርዓተ ማኅበር መልካም አስተዳደር ያለው አቀማመጣቸው ነው።

የቤተ ክርስቲያን ሠርክ ጎብስት

ገንዘብ ሁሉ ቢያንስም ቢበዛም በሠርክ ጎብስት (በዕለት ምግብ) የሚለካ ነው፤ ሠርክ ጎብስት ማለት ጾም ባልሆነ ጊዜ ቁርስም ምሳም ራትም ሆኖ የዕለት ምግብ ይባላል፤ አንድ ባለቤት በቤቱ ከሚጠቀምበት ከዕለት ምግብ በላይ ሌላ ነገር አያስፈልገውም፤ ያስፈልገኛል ብሎ ገንዘቡን ከቤቱ ቢያወጣ ከገዛ ቤቱ ቅሚያ ያካ ሂዳል ማለት ነው።

ሠርክ ጎብስት የቤተ ክርስቲያን ቁመተ ሥጋ ምግብ ነው፤ ምግብ አካላዊ ሕይወት እንደመሆኑ መጠን የበሉት የጠጡት ደም ይሆናል፤ በዚሁም ደማዊ ሕይወት ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው ይኖ ራሉ። በሠርክ ጎብስት የተጠበቀ አእምሮ ጠባይዕም ከንጹሕ አካል ጋር የተገነባ የሰውነት ብርሃን ነው፤ ሆኖም የቤተ ክርስቲያን አንድነት በሠርክ ጎብስት ተጠብቆ የሚኖር ነው።

የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በጥበብ የሚያዝ የአደራ ገንዘብ ነው፤ ያለ መርሐ ግብር ያለ ሥርዓት በማን አለብኝነትና በዘመድ የግል መጠቀሚያ ሲሆንና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ስለሚያ

ፈርስ በምድርም በሰማይም ያስጠይቃል፤ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለሚያላድጉ ተቅዋማት የሚጠበቅ ነው።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ከሠርክ ጎብ ስት ከተሟላ መኖሪያ ቤትና ከተሟላ የክብር ልብስ በላይ ሌላ አያ ስፈልጋቸውም፤ ከደመወዝ ሞያተኛ ከምንደኛው ሠራተኛ ጋር ደመ ወዝ ከተቀበሉና የግል ቤት ከሠሩ ቤተ ክርስቲያን ባለቤት የላ ትም ማለት ነው፤ ገንዘቧ የዓለም ቤተሰብ ማስተናገጃ እየሆነ አን ድነቷ ሲፈርስ ይኖራል፤ አባቶች ደመወዝ እየተቀበሉ ከቤተ ክር ስቲያን ውጭ ቤት ሠርተው ከዚህ ዓለም ሲያርፉ አስከሬናቸው ከመንደር እየወጣ ወደ መቃብር እንደሚወርድ እንጂ ከቤተ ክር ስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባ ትርጉም አይሰጠውም ማለት ነው።

በቁመተ ሥጋ ሳሉ አካላቸው ከመንበረ ጵጵስናና ከመንበረ ፓትርያርክ ግቢ ባይወጣም እንኳ ቤተ ክርስቲያን የተሟላ ሠርክ ጎብስትና የተሟላ መኖሪያ ቤት እያላት ደመወዝ መብላታቸው ከዓለማዊነትና የውጭ ባለሀብቶች ከመባል ነፃ ሊያደርጋቸው አይችልም፤ የገንዘብ ፍቅር መለያየት እንጂ አንድነትና ባለቤትነት አይኖረውም፤ በቤተ ክርስቲያን አንድነትን በሥርዓተ ማኅበር አስ ተዳደር ያልተጠበቀ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የዓለም እንጂ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ሆኖ አይታይም፤ ሆኖም ይህ እንዳይሆን ነው ለቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ማኅበር ሥሪት የተሠራላት፤ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ያለምንም ደመወዝ የቤተ ክርስቲያን ባለቤትነት መብት አላቸው፤ በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ባለቤትነት መሠረት ሌላው የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛም ከሚሰጠው ደመወዝ ሌላ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በከንቱ ለመብላት የሚያመካኝበት ጉዳይ አይኖረውም፤ (የሐ.4፡32፤ 5፡16)

ሥርዓተ አበው የተመሠረተባት ቤተ ክርስቲያን መሠረቷ የሆነ ሥርዓተ አበው ፈርሶ ማንም ባለሥልጣን በሚመጣበት አኳኋን የሚሠራባት ከሆነ ሥርዓት አልባ ሆና በወቀሳና በከሰሳ ትኖራለች፤ ኃላፊነቷን እንድነቷንና የአስተዳደር ሥርዓቷን ተቀብሎ የሚያስተዳድራት ባለቤት ከሌላትም በሚበድላት ዓለማዊ አስተዳደር መነሻነት የፍርድ ባለዕዳ እየሆነች ትገኛለች።

በመሠረቱ የቤተ ክርስቲያን ክብር ታሪክና ዕድገት በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደደር ነው የሚጠበቀው፤ ቤተ ክርስቲያን ርእስ ቅዱስ ፓትርያርክን የምትሾመው የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር መመሪያዋን ካመቻቸች በኋላ ነው፤ ሥርዓተ ማኅበሩ የቅዱስ ፓትርያርኩን ክብር ያስጠብቃል፤ የቤተ ክርስቲያን ክብርና ሞገስ የሆነውን የቅዱስ ፓትርያርክን በዓለ ሢመት በየወቅቱ ያስክብራል፤ በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን መብትና ግዴታ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ብቻ የሚከናወን እንደሆነ ነው የሚታመነው።

አሮጌውን ተውት አዲሱን ልበሱት

ለቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ደመወዝ መክፈል ያስፈለገው በነገሥታትና በመሳፍንት ዘመን ነው፤ የዘመናት ወቅታዊ ሥራ የተለያየ እንደመሆኑ መጠን የማይሻለው ዓለማዊ ሥርዓት ለሚሻለው መንፈሳዊ ሥርዓት ትምህርት ሊሆንና ብዙ መሻሻል ሊገኝበት ያስቻለ መሆን አለበት፤ ዓለማዊነት ወደ መንፈሳዊነት እየተሻሻለ ሲመጣ ሕይወት ይበዛል መንፈሳዊነት ወደ ዓለማዊነት ቢለወጥ ግን ሐሳር ይበዛል።

የዓለማዊ መንግሥት አገዛዝና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተጣምሮ መኖር አልጠቀመም፤ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር

የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አልገነባም እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን የማኅበራዊ ሥርዓት አልባ ሆና እንድትኖርና ከዓለማዊ መንግሥት ጋር በነበራት የአስተዳደር ግንኙነት ምክንያት ዓለማዊ መንግሥት ሲገለበጥ አብራ እንድትገለበጥ ሆነች።

የነገሥታትና መሳፍንት ዘመን አክትሞ ትልቅ መለያየት ከሆነ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ አንድትተዳደር እስከ አሁን ተግባራዊ ያልሆነ የሥልጣን ነፃነት ተሰጠ፤ እስከ አሁን በነፃነት መሥራትና መኩራት ባይገኝም ነፃነቱ ወደኋላ ለመመለስና ከዓለም ጋር አንድ ለመሆን አይደለም፤ በሚያልፍና በሚጠፋ ኑሮ የሚታቀፍ የዓለም ሥራ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አንድነት የለውምና ቤተ ክርስቲያን ተለውጣ ሙሉ አካሏ አንድነት ያለው መንፈሳዊ እንዲሆን ነው።

ቤተ ክርስቲያን ራሷን ትቻል ብሎ መብትና ግዴታን መስጠት ማለት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በነገሥታትና በመሳፍንት ዘመን ጀምሮ የሚበሉትን ደመወዝ አቁመው በባለቤትነት ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ ማለት ነው። (የሐ.20፥18)

የመንግሥተ እግዚአብሔር ሥራ አስተዳደሩ ሙሉ በሙሉ ከዓለማዊነት ተግባር ማለትም ባለቤት ሆኖ ደመወዝ ከመብላት የተለየ ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ቀሰብ የተሟላ ሠርክ ጎብስት (የዕለት ምግብ) ብቻ ነው፤ የቃለ እግዚአብሔር አገልግሎት መዓዛ ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርበው አሳራጊ የሥርዓተ ማኅበር አንድነታዊ አስተዳደር ሲኖርበት ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሲሠራበት የልብን ያደርሳል፤ አለዝያ የቃለ እግዚአብሔር አገልግሎት የዘልማድ ሆኖ ይቀራል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ፍቅር የተያዘ ዓለማዊ አስተዳደር ለደካማው ዓለማዊ ጥቅም የሚሳሳ ከዓለም ጋር የመንግሥተ እግዚአብሔርን ሥራ ተክቶና አሟልቶ የማይሠራ እንዲያውም ርዝራዡን ለመካፈል የቆመ ደካማነት ነው። ሥልጣን እስካለ ድረስ የሚጠቀም ነው፤ ለዘላቂ ሥርዓት መሥዋዕትነት የለውም። የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አባቶች ለሀገረ ስብከቶች ሊመደብ በሚገባ በሠርከ ጎብስት ፈንታ ደመወዛቸውን ለማስተካከል ከየአህጉሩ ይሰበሰባሉ።

ገበሬ ብር አይቈጥርም፣ ጉተራው ነቀዝ እንዳይበላበት ነው የሚቈጣጠረው፤ ቤተ ክርስቲያን ምንጊዜም ሕይወትና ገንዘብ ናት፤ የተሟላ ሠርከ ጎብስትና መኖሪያ ቤት ናት፤ ሁናም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ያለምንም ደመወዝ በባለቤትነት ሲካተቱባት ነው፤ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ናቸው፤ ቤተ ክርስቲያንም ገንዘባቸው ናት፤ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትም የምእመናን ተወካዮች ናቸው፤ ከላይ እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቋት የተልእኮ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። (የሐ.20:28)

ከሠራተኛው አሠሪው፣ ከምንደኛው ባለቤት ይበልጣልና የመንግሥተ እግዚአብሔር ሥራ በባለቤትነት የሚከናወን ነው፤ ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥተ እግዚአብሔር ግብ መምታት ዋና መሣሪያዋ እንደምንደኛ በደመወዝ ሳትለካ የተሰጣት አደራነት ባለቤትነት ነው። ደመወዝ የምንደኛ ዋጋ ሆኖ ቤቱ ንብረቱ የባለቤትነት ነው፤ ምንደኛው ሠራተኛ የሚያድገውም አሠሪ ባለቤት ሲኖርለት ነው።

የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ታማኝ ሐዋርያ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ነውና በመንግሥት እጅ የነበረው

የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ለቤተ ክርስቲያን ሲሰጥ ቤተ ክርስቲያን ሥሪቷ ሥርዓተ ማኅበር እንደመሆኑ መጠን በሥሪቷ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ዓለምን እያስተማረችና ዓለምን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ እያደረገች ለሀገር የምታበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንዲሆን ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣኖች ከቤተ ክርስቲያን ሥሪት ከሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ውጭ በዓለማዊ አስተዳደር ቤተ ክርስቲያን ወደኋላ እያስቀሩ ሀገርን (መንግሥትን) እንዳይበድሉ ነው።

ጊዜው ሙሉ በሙሉ እየተለወጠ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን በነገሥታትና በመሳፍንት አገዛዝ ሥር በኖረችበት ጊዜ ነገሥታት የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ይቀበሉ ነበር፤ በዚህ ምክንያት ነገሥታትና መሳፍንት ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳድሩ ስለነበር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ዝክረ ነገር አልነበረውም፤ የነገሥታትና የመሳፍንት ዘመን ሌላ ለውጥ ተክቶ ሲያልፍ ለውጡ መናፍቃን የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ስለማይቀበሉ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን የምታበዛበት የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ለውጥ መተካት አለበት።

ቤተ ክርስቲያን በጎዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ መድኃኒቷ በክንዷ ነው። ጌታዋ የሰጣትን በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ወንጌል የማስተማርን ሥልጣን በዓለማዊ ሥልጣን ሳትለውጥ ኋላቀር ዓለማዊ ሥልጣንና የግል ጥቅማጥቅምን በሚያስወግድ ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ማደግ አለባት።

‹‹ሕጽግም በብሱዘ ወሰብሰዎ በሐዲስ›› አሮጌውን ተውት አዲሱን ልበሱት እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የቤተ ክርስቲያንን ሠርከ ጎብስት በደመወዝ ስም ይዘው

ወደ ውጭ ሳይወጡና የግል ቤት ሳይሠሩ በተመቻቸ የቤተ ክርስቲያን ሠርከ ጎብስትና መኖሪያ ቤት ተወስነው ያለ ደመወዝ በማኅበራዊ ሥርዓት የአቀማመጥን ለውጥ ካመጡ ‹‹ምስተ ምክብሲተ›› ዓለም መቶ እጥፍ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ እየሆነ ሊመጣ ይችላል። የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ክብርና ሞገስ የቤተ ክርስቲያን ሥሪት የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ነው፤ ሹመታቸው ለባለቤትነት ነው እንጂ ለደመወዝ አይደለም።

ሥልጣን ሰላምና ነፃነት የለውም

ዓለም ሰላም የለውም፤ ሰላምን እንካ ቢሉትም እንኳ አይቀበልም፤ የራሱ ችግር በሚያጋፍጠው ጊዜ በተግባር ሳያምንበት ይበጃል ብሎ ሰላም ሰላም ይላል እንጂ ሰላምን ለማግኘት የእምነትና የተግባር መሠረተ ኃይል የለውም። ዓለም የሰላም ባለቤት አይደለምና ሰላም ከሚገኝበት ቦታ ሰላምን አይፈልግም፤ በማይፈጽመው ሕግ ተደግፎና ሕግን የሥልጣኑ ሞግዚት አድርጎ ሥልጣንን ቢፈልግም በድካሙ ዘመን ሁሉ ሕግ ሲወቅሰውና ሲፈርድበት ይኖራል እንጂ ሰላምን አያገኝም።

ለሰው ልጆች ሁሉ ሰላምን የሚሰጥና ሕግን የሚያስፈጽም የሰላም ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እሱም ሰላም ሰጪ የሆነው በትዕግሥት የዲያብሎስን ኃይል በሻረበት በመስቀሉ ሥራ እንጂ የዚህን ዓለም ሥልጣን ይዞ አይደለም።

ሰላም የመስቀሉ ፍሬ እንደመሆኑ መጠን ሰላምን ማግኘት የሚቻለው ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልዝብ መስቀል ሥር በመቆም ነው። ማንም የሚወደኝ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሌንም ተሸክሞ ይከተለኝ እንዳለው፤ (ማቴ.16፥24)

በቤተ ክርስቲያንም የቤተ ክርስቲያንን ሥሪት የሆነ የሥርዓተ ማኅበርን አስተዳደር የማይመራ ሥልጣን የግሉ የሆነ ቀና አመለካከት ቢኖረውም አይጠቅምም፤ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ኃላፊነትን አይሸፍንም፤ እንዲያውም ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ግብረ ጠልነትን ያበዛል፤ ቤተ ክርስቲያንን በሥልጣን እንድትገዛ እንጂ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ሥራዋን እንዳትሠራ ያደርጋታል።

መሬቷና ንብረቷ ሁሉ ሰብሳቢ ሥርዓት እያጣ በግብረ ጠልነት ዓለማዊ መንግሥት ሊወርሰው ይኖራል፤ በውስጧ ያለው ሥልጣን እስከ ጊዜው ድረስ በርዝራዥ ሲጠቀም ይቈያል። የጋራውን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በተግባር አዳብሮ ለትውልድ አያስተላልፍም። የቤተ ክርስቲያን ሀብት ከእጅ ወደ አፍ አይደለም፤ ‹‹ምስተ ምክብሲተ›› ዓለምን መቶ እጥፍ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የሚያደርግና ጊዜን የሚዋጅ፤ የቤተ ክርስቲያን ሥሪት የሆነ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር መሆኑን ትውልድ ሊያውቀው አልቻለም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ ‹‹*ስናንተ ስለነገርኋችሁ ቃል ስሁን ንጹሐን ናችሁ፤ በስኔ ኦረ ስኔም በስናንተ ቀርንጫፍ በመጸኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሲያፈራ ስንዳይቻለው ስንዲሁ ስናንተ ደግሞ በስኔ ባተኖሩ ስተችሱም። ስኔ የመጸን ግንድ ነኝ፤ ስናንተም ቀርንጫፎች ናችሁ፤ ያስ ስኔ ምንም በታደርጉ ስተችሱምና በስኔ የሚኖር ስኔም በስርሱ ስርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራስ*›› *(ዮሐ.15፥3-5)*

ይህ ዓለም ራሱን ሊያስገዛለት በሚችል ሕይወት ራሱን አያስገዛምና ለሥራ የማይጠቅምበትን ሥልጣን ሊፈልግ ይኖራል። የቤተ ክርስቲያን ሥራ በሥልጣን ኃይል አይሠራም፤ በቤተ ክርስቲያን አንድነት ራሱን ያላስተካከለ ሰውነት የእግዚአብሔርን ሥራ ሊሠራና ሥራው ሊከናወንለት አይችልም።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባቱ ‹‹ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘኪያሁ ሠመርኩ ወሎቱ ስምእዎ›› የምወደው የምወልደው በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት፤ እርሱን እመኑ እርሱን ተከተሉ፤ በእርሱ ተገዙ ሲል እንደመሰከረለት ጌታችን ከዚህ ዓለም ሥልጣን ራሱን ነፃ አድርጎ የአዳኝነት ሥራውን ሠርቶ እንደፈጸመና ለሐዋርያት የሰጠው ሥልጣን ሐዋርያዊ ተልእኮ እንደሆነ ሁሉ ለአዳኝነት ሥራው እንደራሴው በፍቅሩ ሥርዓት የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ናት።

ጌታችንን የባሕርይ አባቱ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እንዳለው ቤተ እግዚአብሔርን ማገልገል ከዓለማዊ ሥልጣን ጋር ስለማይስማማ መንፈሳዊ ሰው ከዓለማዊ ሥልጣን ነፃ ሆኖ በጌታው ፍቅር ራሱን አድኖና ተወዶ ሥራን መሥራት ይበጀዋል፤ አንድነቷን እያፈረሰች ከሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ውጭ በሥልጣን የምትመራ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነቷን በሥርዓት መወጣት አትችልም፤ ፍቅሯና አንድነቷ እየተጓለ ዕድገቷ እያነሰ ይኖራል።

የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በጣም ብዙ ነው፤ አሁንም እንኳ ብዙ ነው፤ ይሁን እንጂ በባለቤቱ በሥርዓተ ማኅበር እጅ ያልተያዘ ገንዘብ የቤተ ክርስቲያን አይደለም። ካለፈው ጊዜ የማይማር እንዲያውም የሚብስበት ሥልጣን የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ከራሱ ጋር የዓለም ቤተሰብ ማስተናገጃ ያደርገዋል እንጂ በአደራነት ጠብቆ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ነው ብሎ አያስከብረውም፤ እስከ አሁን ያለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓለማዊ እንደመሆኑ መጠን ቤተ ክርስቲያን በየወቅቱ የዓለምን

ገፈት ቀማሽ እየሆነች ትኖራለች። ከዓለማዊ መንግሥት ጋር ዓለማዊ ለውጥ ስታካሂድ ትገኛለች ሥልጣን የሚፈጥረው ችግር ነው።

የቤተ ክርስቲያን አንድነት በሥርዓት እንጂ በሥልጣን ቢመጣ ሥርዓት አልባ ሆኖ እያነሰ ይመጣል፤ ሥልጣን የራሱን ክብርና ጥቅምን ስለሚፈልግና የቤተ ክርስቲያን አንድነት የበለጠ ክብሩን የሚጠብቅለት ስለማይመስለው እንዲያውም ጥቅሙንና ክብሩን የሚቀንስበት መስሎ ስለሚታየው የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አይሻም።

ሆኖም ሥርዓት እንጂ ሥልጣን የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ባለቤት ሊሆን አይችልምና ሥልጣን ከሳይ ሆኖ ቤተ ክርስቲያንን ቁልቁል ያያታል እንጂ አብሯት አያድግም፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሊቀ ካህናት ሆኖ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያገለግሉ ሐዋርያትን ይሾማል እንጂ ዓለም እንደሚሾም ዓይነት አይሾምም።

ሥልጣነ ክህነት የተቀላጠፈ ክብርና አገልግሎት ነውና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒት ሆኖ የማገልገል እንጂ የመገልገል ክብር በሌላት በአሕያ ግልገል ተቀምጦ በታላቅ ምስጋና ኢየሩሳሌም ሲደርስ የዚህ ዓለም ሥልጣን የሚመራቸው ነጋዴዎች የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የመነገጃ ስፍራ አድርገውት ሲመለከት ቤቴ የጸሎት ቤት እንደሆነ ተጽፏል እናንተ ግን የሽፍቶች ዋሻ አደረጋችሁት በማለት ገበያቸውን በሥልጣኑ ገለባበጠው እንጂ ከገበያው አልተሳተፈም፤ ትሑት ሊቀ ካህናት ሆኖ አዳነ አገለገለ እንጂ በሥልጣን አልተጠቀመም፤ ቤተ ክርስቲያንም ነጋዴ ወይም መነገጃ አይደለችም፤ የጌታዋን የባለቤትዋን ሥርዓት ተከትላ አገልግሎቷን አክብራ አንድነቷን እንድትጠብቅ ሆና ነው የተመሠረተችው።

ሥልጣን ተራሮችን እስኪያፈልስ ቤተ ክርስቲያንን እገነባለሁ ቢል የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር አመራር ግን ከሌለው ከንቱ ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ስም የሚገነቡ ሕንጻዎችና በቤተ ክርስቲያን ስም የሚሰበሰበው ገንዘብ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ሊሆን አይችልም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሁሉ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር አመራር ካልተያዘ የዓለማዊነት ማስተናገጃ እየሆነና ወደ ዓለም እየተለወጠ ቤተ ክርስቲያንን እያሳነሰ ይመጣል እንጂ የቤተ ክርስቲያን አንድነት አይከናወንበትም፤ (1ኛ ቆሮ.13፥1-2)

ፍሬ ፍሬው ለበሽታ ዓለማዊ ሥርዓት ገለባ ገለባው ለእግዚአ ብሔር እንደተባለው የቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች ተብለው የተሾሙት አባቶች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት እንዲያጠነክር ለሠርከ ጎብስት የሚሰጠውን ገንዘብ በደመወዝ ስም ወደ ውጭ እያወጡ የግልን ቤት መሥራታቸውና የዓለም ቤተ ሰብ ማስተናገጃ ማድረጋቸው ቤተ ክርስቲያንን በሥልጣን ፍቅር ለመለያየት ይጋብዛሉ ማለት ነው።

ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን ማለትም የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር አመራር ከማጠናከርና አንድነትን ከመጠበቅ ሌላ በቅዱስ መጻሕፍት የተፈቀደ አማራጭ የለውም።

ሕግ ወቃሽም፣ ከሳሽም፣ ገዳይም ነው፤ ሆኖ ሕግ ተፈጻሚ ነው እንጂ ፈጻሚ አይደለም፤ የሕግ ፍርድ ሕግን ባለመፈጸም ምክንያት የሚበዛ ከሆነም በመንፈሳዊ ሥርዓት ሕግን መፈጸም ያስፈለገው ሕግ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነገር ቦታ እንዳይኖረው በነገር በመለያየትና በጥላቻ ሰፍኖ እንዳይኖር ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ሕግን በሚጋብዝ ዓለማዊ አስተዳደር ወደኋላ ስትል እንዳትኖር ነው።

ክፍል ሁለት

የቤተ ክርስቲያን ሥልጣነ ክህነትና የክብር መንበር፣ የቤተ ክርስቲያን የተሟላ ሠርከ ጎብስትና የክብር መኖሪያ ቤት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ያለው። ታዲያ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አባቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተሟላ ሠርከ ጎብስት ተወስነው በአንድነት የቤተ ክርስቲያንን ችግር እየፈቱ መቀመጥ አለባቸው እንጂ የቤተ ክርስቲያንን ሠርከ ጎብስት በደመወዝ ስም ወደ ውጭ ለምን ያወጡታል? ደመወዝ ይዘው ከየት ወዴት ይሄዳሉ?

አድልዎ ኃላቀርነት ነው፤ ዓለማዊ አስተዳደር የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር አይተካምና የመጀመሪያው አድልዎ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አስተዳደር ወደ ዓለማዊነት ተግባር ሲያደርሱበት ነው።

እግዚአብሔር አምላካችን በትንቢተ ሚልክያስ ምዕራፍ 3 ቍጥር 10 ላይ በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ወደ ጐተራ ክተቱ ያለው ትንሽም ሆነ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ሲያዝ የአንድነትና የሕይወት ምግብ ይሆናል፤ የቤተ ክርስቲያን ሠርከ ጎብስት በሥርዓት ሲጠበቅ የብዙ ክብርና አንድነት የብዙ ሰላምና ፍቅር መሠረት ይሆናል። ከቁመተ ሥጋ በላይ ያለው የቤተ ክርስቲያን ጥቅም የአንድነት ቀውስ እንደመሆኑ መጠን ጤና የማይሰጥ በሽታ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ያልሆኑ ዓለማውያን የግል ዓለማዊ ሥልጣን እየጋበዛቸው በየዘርፉ ኃላፊነትን እያገኙ የቤተ ክርስቲያንን አህል ውሃ ወደ ውጭ ያግዙታል፤ ይሻረኩበታል፤ በመቀባበል ለግል ጥቅማቸው ያውሉታል፤ ቤተ ክርስቲያን ቁልቁል ስትቀር ትኖራለች፤ በተሳሳተ ዓለማዊ አኗኗር ምክንያት ሰላምንና አንድነትን እያጣች ነው።

ቤተ ክርስቲያን ፍቅርና አንድነት የተጓደለበት የቃለ እግዚአብሔር አገልግሎቷ አሳራጊ ሥርዓት በማጣት ወደ ላይ ሳይደርስ የዘልማድ ብቻ ሆኖ እየቀረባት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ማዳን የሚችለው በቅድሚያ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር አንድነት ንጹሕ መሥዋዕት ሆኖ ሊቀርብለት ነው፤ ከበረት ያልሆኑትን በጎች ወደ በረት ማምጣት በበረት ያሉትን በጎች በሕይወት መጠበቅ ከተቻለ በኋላ ነው፤ (ዮሐ.10÷10

የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚጠነክረው የቤተ ክርስቲያን ቁመተ ሥጋ በመንፈሳዊ ሕይወት እንደሚጠበቅ በሥጋዊ ሕይወትም ሲጠበቅ ነው። ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው እንደሚኖሩ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሀብተ ሥጋ ሁሉ በሥርዓተ ማኅበር ሥር ሲውል ነው፤ ከሠራተኛ አሠሪ ባለቤት ይበልጣልና ምንደኛው የደመወዝ ሠራተኛ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ታማኝ ጠቢብ ሊሆን የሚችለው ያለምንም ደመወዝ በባለቤትነት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ ማኅበር የሚመሩ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አባቶች ሲኖሩለት ነው።

የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ (ሠርክ ጉብስት) ወደ ውጭ ሳይወጣና መንፈሳዊ ክብር ሳይቀነስበት ቤተ ክርስቲያን ከጊዜ ወደ ጊዜ እንድታድግበት ሲደረግ ሥራው የሚያስገኘው ዕድገት የአንድነት ዕድገት እንደመሆኑ መጠን ራስን ለክብር የሚያስገዛና ቤተ ክርስቲያንን የሚያስመሰግን ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያጠቃልል የእግዚአብሔር ቃል እንዳደረጉት ሊሻሻል እንደማይችል፤ አደራነት የተሞላበት የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ (ሠርክ ጉብስትም) እንዳደረጉት ሊሆን የማይችል በሥርዓት የሚጠበቅ የአንድነት መሠረት ነው።

ቤተ ክርስቲያን አብሯት ከተመሠረተ ሥርዓት ውጭ ከኖረች በየጊዜው የዓለምን ገፈት ቀማሽ ትሆናለች፤ ዓለማዊ መንግሥት ሲገለበጥ በንክክ አብራ ትገለበጣለች፤ የዓለም በሽታ እየገባ ሲረ ብሻት ይኖራል፤ የዓለም ሕመምተኛ ትሆናለች፤ ቢሆንም አሁንም ፈውስ በእጇ ነው፤ የአንድነት ሠርክ ጉብስቷን እያጣጣመች በሥ ሪቷ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ከተመራች ትድናለች፤ እንደ ስጦታዋ በተግባራዊ አርአያነቷ የዓለም መድኅን ትሆናለች።

‹‹ዘወየ በሠበ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ቀደስት ወማኅበርነ ውስቴታ›› ማኅ በር አንድነት በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ጸልዩ እያለ እንደሚያ ዘው መጽሐፈ ቅዳሴ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ጸሎት መሥ መሩን ካልለቀቀ ንጹሕ መሥዋዕት ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባልና በሰላም ማሠሪያ የመንፈስን አንድነት ያስጠብቃል።

የእግዚአብሔር ቃል አያልፍም

ዓለም ከራሱ ብቻ ይነሣል፤ የተፈጥሮ መነሻና መድረሻ የለ ውም ፈጣሪውን አያውቅምና ባለቤት የለውም፤ የሚጠፋ የደመ ሥጋ እንጂ የደመ ነፍስ ውበት ሰላምና ብልጽግና አይገኝበትም፤ መዲናዎቹ ክሕደት፤ ኃጢአት፤ ባርነት፤ ድህነት፤ ኋላቀርነት፤ ሥል ጣን መጠላላት መለያየት፤ ውሸት፤ አድልዎና ራስ ወዳድነት ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን አንድነት አለመጠናከር የቤተ ክርስቲያን ስደት ማለት ቢሆንም ትልቁ ነገር ቤተ ክርስቲያን በግል ሥልጣንና ጥቅም የዓለም መድረክ እየሆነች የአንድነቷ መራቈት ችግር ሃይማኖትን ከአማንያን ለውነት አለማስቀረቱ ነው። ዓለማዊነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ እየተመዳደቀ የቤተ ክርስቲያንን

አንድነት ሲያፈርስ ቢኖርም የእግዚአብሔርን ቃል አያስቀርም፤ ቤተ ክርስቲያን ችግሯን መፍታት የማትችልበት ዓለማዊነት ቢሠ ፍርባትም ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ቃል ይለየዋል።

ሕግ ደግንና ክፉውን ለይቶ የሚነግር በቅድሚያ የተሰጠ የእ ግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ መጠን ከሕግ አንዲት ነጥብ እንኳ አትወድቅም፤ ሕግ በሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ካልተፈጸመ ሲፈርድ ይኖራል፤ ሕግ ተሽሮ የኃጢአት መዲና ከመሆንም ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላልና (ማቴ.5፥18) ጌታችን ሕግን ሊፈጽም እንጂ ሕግን ሊሽር አልመጣም።

ከእግዚአብሔር ቃል ከሕግ አንዲት ነጥብ መቅረት ብትችል ኖሮ ሕግ የፈረደውን የሞት ዕዳ በመሥዋዕትነቱ ለመክፈል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ባልመጣም ነበር፤ ሆኖም ሕግ ያልተሻረው እንዲፈርድ ያህል ነው እንጂ ሊያድን አይደለም ‹‹የሞት መውጊያ ኃጢአት፤ የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው›› (1ኛቆሮ.15፥56)

የሕግ ስም ቅጣትና ሞት ነው፤ የክርስቶስ ስም ግን ከሕግ ነፃ የሚያወጣ ሕይወትና ሰላም ነው፤ ሕግን የሚያስፈጽም የሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ነው፤ ሕግን የሚሸፍን የፍቅር መሣሪያና ሕግን ለመ ፈጸም የሕግ ትእዛዝ ለውጥ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሐዲስ ኪዳን ነው፤ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የመዳን ምክንያት ብዙ ነውና ኃጢአት ቢኖርም እንኳ አምላክ እንደ ኃጢአተኛነት ሳይወሰን ለኃጢአት ሥርየት በባሕርይ ልጁ ስም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተችልን፤ በንስሐ መመለስ የሕይወት ነፃነት ነው።

ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ይዞታዋ የእግ ዚአብሔርን መንግሥት ወራሽ ስለመሆኗ ሐዋርያው ቅዱስ ጳው ሎስ ይቃኛል፤ ‹‹ዐገታችን የሚየሱስ ክርስቶስ ስባተ ደማረክ፤ ዓለም ሳይፈ

ጠር በፊቱ ቀዳሳንና ነውር የሴሰን በፍቅር ስንሆን ዘንድ በክርስቶስ ፈጠረን፤ በዐገ ፈቃዱ ስንደ ወደደ በሚየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለስርሱ ልጆች ልንሆን ለስቀ ድሞ መሰነን፤ በውድ ልጁም ስንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን ስደረገ።

በውድ ልጁም ስንደ ጸጋው ባሰጠንነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛችንን ሰገኘንን፤ ስርሱም የበደሳችን ሥርየት ዐጋውንም በጥበብና በሰስምር ሁሉ ሰበዛልን፤ በክርስቶስ ሰማድረግ ስንደወደደ ስንደ ሰሳቡ የፈቃዱን ምሥጢር ሰስታውቆናልና።

በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያሰው ሰሳቡም በሰማይና በምድር ያሰውን ሁሉ በክርስቶስ ስመጠቀለ ነው፤ ስንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ ስንደ ስርሱ ሰሳብ ሰስቀድመን ተመሰንን፤ በክርስ ቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን፤ ይሽውም በክርስቶስ ስስቀድመን ተስፋ ያደርግንና ስኛ ሰክብሩ ምስጋና ስንሆን ዘንድ ነው›› (ሲፌ.1፥3ና 4)።

የባሕርይ አባት ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ‹‹ክሁሉ በሳይ ራስ ስን ዲሆን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ቤተ ክርስቲያን ሰካሱና ሁሉንም በሁሉ የሚ ሞላ የክርሱ ሙሳቱ ስንድተሆን ነው›› (ሲፌ.1፥22ና 23)።

ዘየአሲ ተወካፊ (የሚሰጥ ይቀበላል)

የሥነ ፍጥረት ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ለፍጥረቱ ሁሉን ነገር አመቻችቶ ሰጥቷል ይሰጣልም፤ ‹‹መዘስንበዘ ንስሱ ጸሁብ ፍትወተነ ዘስምፈቃዱ›› ሳንለምነውም እንኳ የሚያስፈልገንን ይሰጠናል።

አምላክ ለፍጥረቱ የሚያስብ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን በስመ ልናደርገው የሚገባንን አስቀድሞ የባሕርይ ልጁን ልኮ አድርጎታል፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስመ የሚያምን

ሁሉ ከኃጢአትና ከሕግ ፍርድ ነፃ የሚሆንበትን አዋጅ በመስቀሉ አውጇል፤ *‹‹ዘየአምን በወልደ ለሕያወት ዘለዓለም››* በልጁ የሚያምን የሚያደርግም የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ (ዮሐ.3፥16)

ይህ ታላቅ መዳን የእግዚአብሔር የጸጋው ስጦታ ነው፤ (ኤፌ. 2፥8) ሰው ለራሱ ደኅንነት ሲል በጸጋ የሚፈጽመው በጎና ማኅበራዊ ሥርዓት ሁሉ ተመልሶ በእግዚአብሔር አምላክ ከጸጋ ስጦታው በኋላ የቤተ ክርስቲያን አንድነት በስሙ እንዲሠምር የሥነ ምግባር ስጦታንም ይቀበላል።

በነቢዩ ሚልክያስ ትንቢት *‹‹በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን ሰሥሬቱን ወደ ጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትባችሁ፣ በረከትንም ለተ ረፍርፈ ባላፈሰሳችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ስለ ስና ንተ ነቀዙን እገሥጻለሁ የምድራችሁንም ፍሬ ለያጠፋም፤ በእርሻችሁም ያለው ወይን ፍሬውን ለያረገፍም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተደሳ ምድር ተሆናሳችሁና ለሕዛብ ሁሉ ብፁዓን ብለው ይጠሩሶችኋል ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር›› (ሚል.3፥10-12)*

እየቃኘ የእግዚአብሔርን አሥራት ከሕዝቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያስገባው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ነው። የቤተ ክርስቲያን አሥራት የቤተ ክርስቲያን አንድነት ሠርክ ጎብስት ነው፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገባው የእግዚአብሔር አሥራት በደመወዝ ለሚሠራው ሠራተኛ አስበ ጻማሁ (የሥራው ዋጋ) ነው። ለአሠሪው ባለቤት ደግሞ ከቤቱ ከቤተ ክርስቲያን ሳይወጣ ሠርክ ጎብስቱ የዕለት ምግቡ ይባላል።

የቤተ ክርስቲያን ባለቤት በደመወዝ ስም ከቤተ ክርስቲያን እየወጣ ሌላ ቤት ማስተዳደር አይችልም፤ ቤተ ክርስቲያን የባለቤትነት ተግባር መውጫና መግቢያ መሠማሪያ ናት፤ ጸሎቷ፣

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን



ማኅበረ ምእመናንን ለማደራጀትና ለማጠናከር

ተሻሽሎ የወጣ

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ

ቃል ማለት ትርጓሜውተለዋጭ ነጋሪ ቃል ። ኢለ፡ቃ፡ዮሐቃ፡ይ፡ይጽፈ። የሐንስ ፩፡ ፲፱፡፰።	አሊስ አበባ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፺ ዓ፡ም በትንሣኤ ዘተላኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መንፈሳዊ ፍትሕዋ፣ አንድነቷና ሥርዓቷ በባለቤነት ተግባር እንጂ በእግረ መንገድ የሚከፍወን አይደለም። የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፡ አባቶች የቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች እንደመሆናቸው መጠን ደመ ወዝ መብላት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የግል ቤት መሥራትና የዓለምን ቤተሰብ የእጎት ወንድም ልጅ ማስተዳደር አይገባቸውም።

በተግባር እንጂ በስም ብቻ የቤተ ክርስቲያን ባለቤት መሆን አይቻልም፤ ሥራ የፈቃደኝነት ደስታ ሊኖርበት የሰውየው ሕይወት ብሩህ ተስፋ አለው፤ በቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ዕርካታ በላይ ሌላ ቤት አይፈለግም፤ በመንፈሳዊ ፍቅር ኃላፊነትን በመወጣት ራስን ከወቀሳ ነፃ ማድረግና ቤተ ክርስቲያንን ማሳደግ ይቻላል፤ ቤተ ክርስቲያን ጊዜን መዋጀት የምችለው የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ሥነ ምግባሯን ስታሳምር ነው።

ቃለ ዓዋዲ፡- ቃለ ዓዋዲ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ግንብ እንደመሆናቸው መጠን የአንዲት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ወይም ማኅበረ ምእመናን ተብለውበት በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተባባሪነት ለቤተ ክርስቲያናቸው የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ለማዳበር፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅና መንፈሳዊ አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ለማሻሻልና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከታት በማናቸውም ጉዳይ ራሷን ለማስቻል፤ ምእመናንን ለማብዛትና እንዲሁም በመንፈሳዊ ዕውቀት ጐልምሰው በምግባርና በሃይማኖት ጸንተው በክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖሩ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት እንዳይባክን ለመጠበቅ እንዲለማና እንዲያድግ ወዘተ ለማድረግ ተሻሽሎ የወጣ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ ነው፤ (ም. 2 አንቀጽ 5)

ሆኖም በአንጻሩ ከመሳፍንት ተያይዞ የመጣው ዓለማዊ አስተዳደር ተለውጦ የቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት በመንፈሳዊ ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር አስካልተዋቀረ ድረስ ይህ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን በሚያዋቅር ረቂቅ የተዘጋጀ ቃለ ዓዋዲ የሚፈለገውን ያህል ተፈጻሚነት አይኖረውም። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ግንባታ ሥርዓተ ማኅበር እንደመሆኑ መጠን ያለ ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ማለት ያለ አስፈጻሚ በቃለ ዓዋዲ ስም ብቻ የሚካሄዱ ሥራዎች ምን ያህል ወደኋላ እንደሚቀሩ እንመለከታለን።

ቃለ ዓዋዲ የምእመናንን አስተዋጽኦ ለማስተባበር የተዘጋጀ መመሪያ ነው እንጂ ጠቅላይ ቤተ ክህነትን በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ያዋቀረ አይደለም። ምን ጊዜም የቤተ ክርስቲያን ኃላፊና ጠባቂ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ሆኖም የጠቅላይ ቤተ ክህነትን የሥራ ድርሻ ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻውን እንዲሠራበት ማድረግ ካለው ኋላ ቀርነት የሚያድን ለውጥ ስለማይታይበት የቅዱስ ሲኖዶስ አንዱ ኃላፊነት መመሪያን በማውጣት እንደ ሐዋርያት በቀኖናና በስብከተ ወንጌል ተልእኮ ጠቅላይ ቤተ ክህነትን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ማደራጀት ነው።

ጥቅማቸውና ክብራቸው የሚነካ እየመሰላቸው የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ህልውናን የማይፈቅዱ ግለሰቦች ቢኖሩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር የዓለማዊ መታለል ኋላ ቀርነትን የሚያስወግድ ደረጃ በደረጃ መንፈሳዊ ክብርንና አጥፍ ድርብ ሥጋዊ ጥቅምን የሚያስገኝ መሆኑንና ቃለ ዓዋዲውም ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር አር አያነት ብቻ ተፈጸሚነት እንደሚኖረው መረዳት ይችላሉ።

ሁለገብ መንፈሳውያን ምሁራን ለቤተ ክርስቲያን እንደሚያስፈልጉ ይታመናል። ይሁንና በቤተ ክርስቲያን የምሁራን ሙያና ዋጋቸውን የሚሸፍን መንፈሳዊ እርካታን የሚሰጥ በግል ሥልጣን አስተዳደር የተቆራኘ ጠባብ አስተሳሰብ ሳይሆን የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሥራትና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር መውደድ እጅግም ከራስ ጥቅም የቤተ ክርስቲያንን ጥቅም ማስቀደም ማለት ሳይሆን ስለ ራስ ጥቅም ማሰብ ማለት ነው። ሆኖም የቅዱስ ሲኖዶስ ኖላዊነት (ጠባቂነት) በአዲስ መልኩ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር በኩል ለምእመናን የሚተላለፍ መሆን እንደሚገባው መጠን የሥርዓተ ማኅበርን አስተዳደር መመሥረትና ማመቻቸት አለበት።

የገበሬ መልካም አስተዳደር

ጠንቃቃ ገበሬ በበጋ መሬቱን አለስልሶ ክረምት ሲገባ መርጦ ያስቀመጠውን ምርጥ ዘር ይዘራል፤ በጭንጫ ላይ ሳይሆን በለስላሳ መሬት የዘራው ዘር ይበቅላል «ሠምጎ ለሐዱ» አንዱ ዘር ሠላሳ፣ ስልሳ፣ መቶም እንዲያፈራ ያድጋል፤ ያፈራልም፤ ገበሬ የድካሙን ዋጋ ያገኛልና የዘራውን ያጭዳል፤ ሁሉም በሥራ ኃይል የሚገኝ በረከት ነውና በገበሬ ሥራና ፍሬ የተመሰለው የመንግሥተ እግዚአብሔር ሥራ ብዙ ሠራተኞች ያስፈልጉታል፤ ሠራተኞቹም ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ውጭ ያልሆኑ፣ ዓለም የማይገዛቸው፣ መንፈሳዊ ነፃነት ያላቸው ሠራተኞች መሆን አለባቸው፤ ሁሉ አይታመንም የሚታመን ለራሱ ሲል የታመነ ይሆናል፤ ለኃላፊነቱ ፍትሕ የማይኖረው ግን ምንደኛ ነው።

ገበሬ ሲያርስ፣ ሲቆፍር፣ ሲዘራ፣ ሲያጭድና ሲለበልብ ውሎ ወደ ቤቱ ሲገባ የተገባው ምግብ ይቀርብለታል ይመገባል፤ ኑሮው በዕለት ምግብ ብቻ የተመጠነ ነው፤ የገበሬ ባለቤትነት ከሠርክ ጎብስት ከዕለት ምግብ አያልፍም፤ ሀብቱ ሲበዛ ከቤተሰቡ ጋር ሠርክ ጎብስቱ የዕለት ምግቡ እየተሻሻለ፣ ቤቱ እያማረና እየተስፋፋ ይመጣል፤ መንጋው ይረባለታል፤ ማዕዱ እየበረከተ ከእንግዳ ጋር እንጀራ ሲቈርስ ይኖራል፤ ከሚተማመንበት ቤቱ ሀብቱን በደመወዝ ስም ወደ ውጭ አያወጣም።

ቤቱ የራሱ ግርማ ሞገስ ነውና የክብር ቤቱን ከመንከባከብ ወደኋላ አይልም፤ ቤቱ ቢሞላም እንኳ በቃኝ አይልም፤ አንድም ቀን ሥራ አይፈታም፤ ገበሬ ኃላፊነቱን በእምነት የሚወጣ የሰላም ባለቤት ነው፤ ቤተ ክርስቲያንም ለመንግሥተ እግዚአብሔር ለወንጌል ሥራ ባለቤት ናት፤ ወደኋላ የሚላት ዓለማዊ ሥርዓት አልተሠራላትም።

ዓለም በሥራ ጠባይ መዛመድ እያቃተው በሥልጣን ሽኩቻ ሲፋጅ እንደሚኖር ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ከሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ውጭ ሥልጣን ሰፍኖባት ከኖረ ለራሷ ዕድገትና ለሀገር ሰላም አብነት መሆንና ጊዜን መዋጀት አትችልም፤ ማንም ሰው ሳይሠራ እንደማይበላ ዓይነት ሁሉ ፍትሕ የሌለው ኑሮም ሰላምና አንድነት አይገኝበትም፤ የዓለም ጦም አዳሪ ያደርጋል።

ሐዋርያት ሂዱና አስተምሩ ተባሉ፤ ከታዘዙት በቀር ሌላ ዓለማዊ ችግር የለባቸውም ነበር፤ ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና እንደ ጊዜው ሁኔታ ከእግዚአብሔር ረድኤት የሚያገኙትን በጎብረት እየተመገቡ ሲያስተምሩ ግዳጃቸው አንድ ወጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስተማር ነበር። ቃሉ እንደሚናገረው ለመንግሥተ እግዚአብሔር ሥራ የሚበጁትን የሥርዓተ ማኅበር ተግባሮችን ያከናውኑ ነበር።

ሆኖም ነቢያት የዘሩትን የእግዚአብሔር ቃል ሐዋርያት አጨዱት፣ ሰበሰቡት፤ ዕድለኞች ሁነው በአንድነት ቤተ ክርስቲያንን መሠረቱ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው ይገቡ ነበር እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ይዘው አይወጡም ነበር፤ ዓለም እስካለንገደፃቸው ድረስ ሁሉም ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ይጠቀሙበት ነበር።

ቤተ ክርስቲያን በወሬ፣ በሥልጣን ፍላጐትና በመናፍቅነት እን ዳትፈታ አንድነታቸው ይጠብቃት ነበር። ዓለም መንፈሳዊ መግባ ባት ስለሌለው ሕግና ሥልጣን ያስፈልጉታል፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ዳግም ተወልዳ መንፈሳዊ መግቦት አላትና የፍቅር ምሳሌ ናትና በዘመኑ ሥልጣንና የሥልጣን ምግዚት የሆነው ሕግ አያስፈል ጓትም ነበር፤ በሥነ ምግባር የተጋች ነበረችና ሕግ በነገር አይጠቀ ምባትም ነበር፤ *‹‹ኃጢአት ሰይገዛችሁምና ከሀጋ በታች ስንኗ ከሕግ በታች ሰይኖ ሳችሁምና››* እንዳለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያት መልእ ክተ ሕግ ሁነው ይሠሩ ነበር። (ሮሜ.6፥14)

ከሕግ በላይና ከሕግ ነፃ የሚያደርገው ሥርዓት ነውና አሁን ቤተ ክርስቲያን ኋላቀር የምትሆነው በገንዘብና በሰው ማነስ አይ ደለም፤ በሥርዓት አልበኝነት ነው። ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት የማይገዳቸው ምንደኞች በቤተ ክርስቲያን የሚበዙት በሥልጣን ጊዜ እንጂ በሥርዓት ጊዜ አይደለም። ያለ ማኅበራዊ ሥርዓት በባ ለሥልጣን ትሩፋት ቤተ ክርስቲያን መሻሻልና ዕድገት አይኖራትም።

ሥልጣን አንድነት ስለማይስማማው አንድነትን ያፈርሳል እንጂ አይገነባም፤ እንደ ባሕርዩ ቤተ ክርስቲያንን የዓለም ቤተሰብ የባልና የሚስት መሥሪያ ቤት ያደርጋል እንጂ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚፈይድበት የሥርዓተ ማኅበር አቋም የለውም።

በአንጻሩ ግን የቤተ ክርስቲያን አንድነት ሥልጣንን ያስወግ ዳል እንጂ ሥልጣንን አይሻም፤ ቤተ ክርስቲያን በማኅበራዊ ሥር ዓት አንድነቷን ስትጠብቅ ለሁሉም ዜጋ የሚሆን መንፈሳዊ

ፍትሕ ይኖራታል፤ ሥራና ሠራተኛም ይበዛላታል፤ እግዚአብ ሔር መንፈስ ቅዱስም አብሯት ይሠራልና ሥልጣንን አትሻም።

ሆኖም የግል ሥልጣን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ አንድነትን ሊያፈርስ የማይችለው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተ ዳደር እስካለ ድረስ ነው። ዓለማዊነት ሕግና ሥልጣን ቢገዙትም፤ ቤተ ክርስቲያን በጥበብና በአእምሮ ጠባይ ያደገች፣ ሐዋርያት ያሠለጠኗት እንደመሆኗ መጠን ወደኋላ ለሚላትና አንድነቷን ለሚያፈርስ ሥልጣን መገዛት አይገባትም።

ዓለም ቢያለማም ቢያጠፋውም ከሥራው ተለይቶ አይታይም፤ ሁልጊዜ ሥራውን ቢሠራ እግዚአብሔርን ግን ባያውቅ ቤተ ክር ስቲያንም የመንግሥተ እግዚአብሔር ወንጌል ኃላፊ ብትሆን ኃላ ፊነቷን በሥርዓት ባትፈጽም ግን ከዓለም የተለየ ሕይወት የላት ምና ከዓለም ጋር ታልፋለች ማለት ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ሥራን የሚ ያሠራት አንድነቷን በሠርክ ጎብስት መገንባት ሲኖርባት ነው።

ተማሪ የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ እንዲለብስ ይደረጋል፤ ሆኖም መማር አለበት፤ ካልተማረበትና ካላወቀበት ግን ኋላቀር ይሆናል፤ ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ ለባለቤትነት ተመርጠው የሚ ሾሙት ከሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ሠርክ ጎብስት ይልቅ ደመ ወዝ ይላሰናል ብለው በደመወዝ መኖርን ቢመርጡ ያነሰውን መር ጠዋልና ለቤተ ክርስቲያን የተመደበ ተግባራቸው ሁሉ ኋላቀር ነው፤ መጨረሻውም ሞት ነው።

የአንድነት መሠረትና ሕይወት የሆነው የቤተ ክርስቲያን ሠርክ ጎብስት ከቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጋር ሲያጣጥሙት ዝግ ጅቱ ተሰብስበው እንደሚመገቡት ዓይነት ብቻ አይደለም፤ በየክ ፍሉ መኖሪያ ቤት እንደ ፍላጐት በፕሮግራም እየተዘጋጀ የሚቀ ርብ የክቡራንና የጠቢባን ሥርዓት አዘል ምግብ ነው።

ግብረ ጠልነት ምንደኛነት ነው

የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ያልተመሠረተባት ቤተ ክርስቲያን ለውስጥም ለውጭም ምሳሌ መሆን የምትችልበት መልካም የአስተዳደር አርአያነት አይኖራትም።

በየመሥሪያ ቤቱ የሠራተኛ ክበብ እንዲኖር የተፈለገው ምን ጊዜም የሀገር ዕድገት የሠራተኛ ዕድገት ነውና ሠራተኛው በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲጠቀምበትና ወዲያውም ክበቡ የጊዜውን የኑሮ ውድነት የሚቋቋም የጥሩ አቅርቦት ዕድገት እንዲኖረው በየመሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት እንዲሠራበት እንጂ ከጊዜው የኑሮ ውድነት ጋር የሚታገል የውጭ አትራፊ ነጋዴ እንዲጠቀምበት አይደለም።

የቤተ ክህነት ምንደኛነት ይዞ መሄድን እንጂ የሚውልበት ቦታ ወርቅ የሚዘንብበት መሆኑን አያውቅም፤ በሥርዓተ ማኅበር አንድነት ያልተገነባች ቤተ ክርስቲያን በምንደኛ ተግባር ወደኋላ መቅረት ተግባሯ ይሆናል።

ዓለም አተርፍ ባይ አጉዳይ ነውና ቤተ ክርስቲያን በሥሪቷ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር የሚመራት ባለቤት ስለሌላት የቤተ ክህነት ምንደኛ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች የክበቡ ማኅበራዊ ጥቅም የቤተ ክርስቲያን ማለትም የራሳቸው መብትና ግዴታ መሆኑን አልተገነዘቡትም።

የቅርቡ ማኅበራዊ ጥቅም እንደ ትልቅ ቁም ነገር ካልታሰበበት ከሩቅ ያለው የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ገቢ ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትና አንድነት እንዲበጅ የሚያስችል ዋስትና የለውም ማለት ነው። መንፈሳዊ ስም ያለው የዓለም ቤተሰብ የባልና ሚስት መሥሪያ ቤት ፍትሕ መንፈሳዊ አይገኝበትም።

የሠራተኛው ክበብ ማኅበራዊ ተግባር ለውጭም ለውስጥም መልካም ምሳሌ እንዲሆን መሥሪያ ቤቱ እንዲሠራበት ካልተፈለገና ክበቡ የውጭ ነጋዴ ተከራይቶ እንዲነግድበት ከተደረገ ቤተ ክርስቲያንም ጠባቂ ሥርዓት የላትም ማለት ነው።

ነጋዴው የቤት ኪራይ ከፍሎ በኑሮ ውድነት ጊዜ ለማትረፍ ያህል የሚያቀርበው መስተንግዶ ከሠራተኛው ጋር ምን ያህል ሊመጣጠን ይችላል? ቤተ ክርስቲያንስ የምትጣጣመው ከምን ዓይነት ማኅበራዊ ስነ ምግባር ጋር ነው?

በማኅበራዊ ሥርዓት ተግባራዊነት መልካም ምሳሌ ሊሆን የሚገባው የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሠራተኛን ክበብ በግብረ ጠልነት ለውጭ ነጋዴ ማከራየት ምንደኛነት ነው፤ የማኅበራዊ ሥርዓት አስተዳደር ያልተጠበቀበት ግቢ ምንደኞች እንጂ ባለ ቤቶች አልተሠማሩበትም ማለት ነው። ራስን ለሕይወት ታሪክ መጥቀም የሚቻለው በግል ጥቅም ሳይሆን በሚመተ ክህነት ሥራ የቤተ ክርስቲያንን አካል መርዳት ነው፤ በግል ጥቅማ ጥቅም እንደ ሚጨረጭሱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ኃላፊዎች ተግባር አይደለም።

ሠራተኛ በተሠማራበት ቦታ ሥራውን ሲፈጽም ነው ጥቅሙንና ታሪኩን ማስከበር የሚችለው። ለሥራ የተሠማሩበትን ቦታ በምንደኝነት መበደልና አሳልፎ መስጠት ብልጠት ሳይሆን ዓለ ማዊ ሞኝነት ነው፤ ማኅበራዊ አህል ውሃ የቤተ ክርስቲያን አንድ ነት ምሰሶ እንደመሆኑ መጠን ቤተ ክርስቲያናችንን በማኅበራዊ ሥርዓት ማስተዳደር ብዙ ትርፍ እንዳለው በነጋዴ ሥራ የተመ ሰለ፣ በአርአያነቱ ምእመናን የሚበዙበት ማኅበራዊ ሥራ ነው።

ምእመናን እየበዙ የሚመጡት የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ስነ ምግባሮች ተግባራዊ እየሆኑ ምሳሌነት ሲኖራቸው ነው፤ ድሮ ዕውቀት ተግባራዊ ነበር፤ ዛሬ ግን ወደኋላ የሚያስቀር የሥል

ጣንና የግል ጥቅም መሣሪያ እየሆነ በመምጣቱ የዕውቀት አሮ ጌም አለው ማለት ነው። ቢሆንም የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሠራተኛ ክበብ የነጋዴ መብት ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ሥርዓት መሠረት የሠራተኛው መብትና ግዴታ ነው።

እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው ‹‹መከሪከሙ ሊተሰምረ ኀበ ሰሐዉር ወተሰምረ ፍኖቶ›› እናንተ የም ሄድበትን አታውቁም፣ መንገዱ ግን ታውቃላችሁ፣

‹‹ወይቤሉ ቶማስ እግዚኦ ዘኢነአምር ኀበ ተሐውር በስፎ እንከ ነአምር ፍኖቶ›› ቶማስም አቤቱ የምትሄድበትን የማናውቅ እንግዲህ መንገ ዱን እንዴት እናውቃለን አለው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እን ዲህ አለው፤ የእውነትና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ፣ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። (ዮሐ.14፥4-6)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹መቼም ለይሁድ ምልክትን ይሰምናሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብ ካለን›› ይላል (1ኛቆሮ.1፥22-24)

ቤተ ክርስቲያን የምትድንበትና የምትሰብከው የዚህ ዓለም ጥበብ ያልሆነ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ሕግ በክርስቶስ ብቻ ተፈጸመ ማለት የሚያሳስት የሕግ ተመጻዳቂ ሰይጣን ዲያብሎስ በመስቀል ኃይል ድል ሆነ ማለት ነው። ይሁን እንጂ ዓለም ዕረፍተ ሥጋና ዕረፍተ ነፍስ የለውምና ነገረ መስቀል ከነገረ ዓለም ጋር ቢቀላቅ ሉት ሰላምን አያስገኝም የዓለምን ችግር ሁሉ ሊያስወግድ አይ ችልም፤ መርህ የለውም የሰላምን በር ማነፅ አይችልም።

ዓለም ምልክትን ቢፈልግ ቤተ ክርስቲያን በልቧ የያዘችውን የሰላም ባለቤት መድኃኒቷ ኢየሱስ ክርስቶስን ሰብካለች፤ ለምሳሌ ሕግ ይፈርዳል እንጂ ጊዜን አይዋጅም፤ የቤተ ክርስቲያን አመ ሠራረት ግን የሕግን ኃይል የሚያስቀር የመስቀሱን ሰላም ለመስ በክ ነው፤ ጊዜን እንድትዋጅ ነው። ዓለም እስኪያልቅለት ድረስ ሥጋዊ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ግን የማታልፍ መንፈሳዊ ናት፤ ዓለም ምድራዊ ብቻ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ናት፤ ሆኖም የዓለ ምና የቤተ ክርስቲያን አቀማመጥ የተለያየ ነው። በመንፈሳዊ ሥር ዓት አስተዳደር ሊኖሩ ሥርዓቱ ሕግን ያስፈጽማል፤ ከሕግ በላይ ከጸጋ በታች ለመሆን ያስችላል፤ ከሕግ ነፃ ያደርጋል።

የዓለም ሥልጣን ሕግን ያጠነክራል እንጂ ሕግን አይፈጽ ምም፤ ያልተፈጸመ ሕግም ዓለምን ይፈርድበታል እንጂ ጠብቆ አያ ድነውም። የሕግን ፍርድ የሚያበዛ የሕግ ተመጻዳቂ የዲያብሎስን ፈተና በክርስቶስ መስቀል ድል ማድረግ የሚቻል ከሆነም ሐዋ ርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ንህነሰ ነሰብክ ክርስቶስሃ ዘተሰቀለ›› እኛስ የተ ሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን ብሏል። የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክና ቤተ ክርስቲያንን ማሳደግ የሚቻለው ከዓለማዊ አስተዳ ደርና ተግባር ተለይቶ ነው፤ የዓለምን ኋላቀር ውስብስብ ነገር አስቀርቶ ነው።

ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ በክህነት ስለተሾመባት ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲጸልይ ‹‹ሰባት ዘይ ዓለም ሰንተ ስንደባስኝ በመደድከኝም መጠን ስነርሱን ስንደመደድካቸው ያውቃል›› እንዳለው ዓለም እግዚአብ ሔርን ማወቅና ማመን ማመስገንም የሚችለው ቤተ ክርስቲያን በአርአያነት በምትሰጠው በተጠናከረ የቅርብ አገልግሎት ምክን ያት ነው።

እንደ ሐዋርያት ለምንደኛ ከሚሰጥ ደመወዝ ነፃ ሆኖና ከዓለማዊ አቀማመጥ ተለይቶ በተሚላ ሠርከ ጎብስት የቤተ ክርስቲያን ባለቤት መሆን ነው፤ ይህም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አባቶች ኃላፊነት ነው፤ የሁሉም ተግባር አይደለም፤ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ *‹‹ስንዚህን የሰጠሽኝን ዘዓለም ስንድተጠብቃቸው ስንጂ ዘዓለም ስንድታወጣቸው ለዐበምንህም››* እንዳለ ሁሉ በዓለም መኖር ዓለምን ለማሸነፍ ነው፤ (ዮሐ.16፥15)

ሥልጣን በሐዲስ ኪዳን ዘመን አሮጌ ሥርዓት ነው

ልጅ በቅንነት እንደሚታዘዝ እግዚአብሔር በፍጹምነት የሚታዘዘውን የባሕርይ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮ ሲሾመው ቤተ ክርስቲያንን በደሙ *ስንዲመሠርታት ‹‹ለንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከጼዴቅ››* አንተ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት የዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ ነው። (መዝ 104)

ሁሉንም ፍትሐዊ ሥራ ይወስነዋልና የክህነት ሥራ የቤተ ክርስቲያንን የአስተዳደር ሥርዓት ይበይናል፤ ይኸውም የሐዋርያት ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ነው፤ ፈቃደኝነት የተከተለውና የተቀላጠፈ የክህነት ሥራ ራሱ ሕይወትና ሰላም እንደመሆኑ መጠን ድካም የለበትም፤ ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚታቀዱ ሥራ ዎች ሁሉ ሕይወትና ሰላም ናቸው። በሥልጣንና በኋላ ቀር ጥቅም ሊፋጁ እንደመኖር አይደለም፤ ከዚህ ዓለም ሥልጣንና ተግባር ሁሉ ተለይቶና አርፎ መቀመጥ የመዳን ሥራ እንቅስቃሴ ነው። የዓለማዊነት ድካም ያልተጫነው የመልካም መንፈሳዊ አስ ተዳደር ዋና አብነት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሠረ ክህነት ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *‹‹ለባቱ ስለስ ለሁን ይሠ ሬፀ፤ ስኔም ስሠሬለሁ ዮሐ.5፥17 ስናንተ ደካሞች ሸከማችሁ የስበደ ሁሉ ወደ ስኔ ኑ ስኔ ስሳርፋችኋለሁ፤ ቀንበሬ ፀዝብ ሸከሚም ቀሲፀ ነውና ስስኔ ተማሩ››* ይላል። ይህ ጥሪ ከሞት ድካም የሚያሳርፍ ዘላለማዊ ሕይወት የሚሰጥ ለዓለም ድካም ተገዢ ከመሆን የሚያድን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር የሠራው ሥራ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ከሥል ጣን ነፃ የሆነ ዓለም ወደኋላ ሊያስቀረው ያልቻለ የሕይወት ሥራ ነው።

የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሾመበትን ሥራ የባሕርይ አባቱን ፈቃድ ብቻ ሊፈጽም ተሾመ፤ የተሾመም እንደ ሥርዓቱ ይሾማልና ጌታችን ሹም የላካቸው ደቀ መዛሙርት ክህነታቸው የተቀላጠፈ የተልእኮ ሹመት ነበር፤ ማቴ.10፥1 የመንግሥተ እግዚ አብሔርን ሥራ መሥራት የሚቻለው በዓለማዊነት ጠባይ ሳይወ ላውሉ ነውና ሐዋርያት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ወንጌልን አስተምረው በመድኃኒቷ ስም ቤተ ክርስቲያንን መሠረቱ።

‹‹ዝናቸው ወደ ስገር ሁሉ ወጣ›› እስከ ዓለም ዳርቻም ድረስ መንፈሳዊ ሕይወት በዛ፤ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ከፍ አለች፤ ቤተ ክርስቲያን አንድነትንና መንፈሳዊ ሕይወትን ከሚገነባ ከማኅበራዊ ሥርዓት ጋር ነው የተመሠረተችው በባዶ አልተመሠረተችም።

ሐዋርያት ዓለማዊ ሥልጣን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ ችግር እንዳይፈጥርባቸው በጋራ የተመሠረተ ወሰኑ እሳት መሐሉ ገነት የሆነ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር መመሪያ ነበራቸው። እስከ አሁንም እስከ መቼውም የቤተ ክርስቲያን መመሪያ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ሆኖ ይገኛል።

ስለሆነም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ደመወዝ ከመብላት ነፃ ሆነው በሥዓተ ማኅበር አስተዳደር ባለቤትነት የእግዚአብሔር ቃል እንዲነግሩ፤ የመማርና የማስተማር፤ የልማት፤ የሕክምና አገልግ ሎትና የቴክኒክ ሞያዎች መሪዎች እንዲሆኑ የሰማይና የምድር

ክብራቸው የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብና ንብረት እንዲያ ስጠብቁ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሥሪቷ የሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ባለቤትነት እንዲኖራትና ዓለማዊ ሥልጣን እንዳይገባባት መከላከልና መታገል ይኖርባቸዋል።

ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሊቃውንት፣ ቀሳውስት መዘምራንና ዲያቆናት መሰል ምእመናን በሥርዓተ ማኅበሩ ሥርዓት ውና ወሰናቸው በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር የተመጠኑ እንዲሆን ነው፤ ሥርዓተ አበው የሚያዘው የሐ.5፡32-36 የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ሲጠናከር ነው አንድነትን የሚያፈራርስ ሥልጣን ሊወገድ የሚችለው።

የቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ሥርዓት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመሠረተ እምነት ይህ ጉደላት ይህ አነሳት የማትባል ሕገ ኦሪቱንና ሕገ ወንጌሉን አጣምራ የያዘች ምልዕት ናት።

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚሰፍር ጉልቁ ዘመን የዘመናት መሥፈርት (ባሕረ ሐሳብ) አላት፤ በየ ዓመቱ በመጥቅዕ እየተሰዋወጡ የሚገኙ የጌታችን አበይት በዓላ ትንና አጽዋማት ታከብራለች ታዘክራለች።

<u>ሃይማኖት</u>፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቧን የምትመራበት ቅዱሳት መጻሕፍት የመሰከሩበት አካላዊ ቃል ወልድ ዋሕድ የሚለው ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የወሰኑት የሃይማኖት ጸሎት ትርጓሜን ታስተምራለች።

<u>ከታሪክ መጽሐፍ</u>፡- እገሌ ምን ሠርቶ አለፈ ይባላልና አለቃ ኪዳነ ወልድ የተባሉ ታሪክ ጸሐፊ ሲጽፉ ራስ ወልደሥላሴ ትግራይን ሲገዙ ከትግራይ ገዳማት ከአንዳባ ገሪማ ገዳም አባ ኪኑ፣ ከደብረ ዳሞ አባ ቃሉ፣ ከተንቤን አባ በትሩ የተባሉ ሦስቱ ተነሥተው ጸጋ የነበረውን ተዋሐደ ብለው ሰይመው እስከ አሁን በዚህ ይሠራበታል ሲሉ ጸጋ የሚባለውን በመደገፍ የግእዝ መዝገበ ቃላት በሚል መጽሐፋቸው ጽፈዋል፤ (ገጽ 491)

ጸሐፊው ቢጠሉም ቢወዱ ጽሑፋቸው የትግራይ ገዳማት ሊቃውንት ሲኖዶስ እየሆኑ በቀደምትነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምርበትን ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት የወሰኑትን የጸሎተ ሃይማኖትን ትርጓሜ እያስተማሩና እያጠናከሩ ቤተ ክርስቲያንን በአደራነት ጠብቀው ለትውልድ ያስተላለፉ የቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች መሆናቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ ነው ማለት ይቻላል።

መጽሐፋቸው የመንቀፉ ጉዳይ ሳይሆን የትግራይ ገዳማት ዝክረ ታሪክ በመያዙ ትልቁን ነገር ያሳያል፤ ታሪክ ሰው የማያስቀረው መንፈሳዊ ነውና የሃይማኖት ወይም የእምነት ባለቤትነት ትግል ታሪክና ቁም ነገር ከነቃፊም ሊገኝ ይችላል።

<u>የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት</u>፡- ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸው የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም የሚፈተትበት (የሚዘጋጅበት) የታቦተ ሕጉና ምስለ ፍቁር ወልዳ (የሥዕለ አድኅኖ) መንበር የተቀመጠበት ምስዋዕ መቅደስ፣ ቅድስት፣ ቅኔ ማኅሌት ሆኖ በተለያየ ቅርፅ የታነጸ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንና ቅዱሳት መጻሕፍት፣ አዋልድ፣ ልብሰ ተክህኖ (የክህነት ልብስ)፣ ጻሕል፣ ፅዋ፣ ፅንሀህ፣ ዕጣን፣ ጧዋፍ፣ ሻማ፣ ቀንዲል፣ ከበሮ፣ ፀናፅል፣ መቋሚያ ወዘተርፈ ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አካል፡- ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበት የመንፈሳዊ አካል ሥርዓት፣ ፊደል፣ ግእዝ ንባብ፣ ውርድ ንባብ፣ ጥቅል (ቁም) ንባብ፣ የቃል ትምህርት በንባብና በዜማ፣ ያሬዳዊ ፀዋትወ ዜማ ግእዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ ቅኔ፣ ማኅበራዊ ሥርዓት፣ እምነት ክህነት ተራዳኢነት፣ (ዲቁና) ምንኵስና፣ ቁምስና፣ ኤጲስ ቆጶስነት፣ ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክነት፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ጾም፣ ጸሎት፣ ንስሐ፣ ስሬት ወዘተርፈ ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፡- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ *‹‹በዘተውህበ››* የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ግን አንድ ነው እንዳለው የሠራተኛው የአገልግሎት ችሎታ የተለያየ ነው፤ ሰባኪው ወይም አስተማሪው ቀዳሽ ይሁን ደካማው ብርቱ ካልሆነ ሳይባል በሠራተኛው ዘንድ የማግለልና የመገለል ተጽዕኖ ሳይኖር ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ አገልግሎት ባለው የሠራተኛ አንድነት ትገነባለች፣ ትገለገላለች።

የውጭ ሃይማኖት ተከታዮች ሳይፈቀድላቸው የኢትዮጵያ አር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቃለ እግዚአብሔር መገልገያ ዎች ንዋያተ ቅድሳት ከበሮን፣ ፀናፅልን፣ መቋሚያንና ቅዱሳት መጻ ሕፍትን የአቋቋም ደብተራውንም ከገበያ እያገዙ ከቤተ ክርስቲያና ችን ያላቸውን ልዩነት ያስተምሩባቸዋል፤ የመንፈስ ቅዱስ (የሥ ላሴ) ልጅነት በእምነት ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ሽፋን እየተለወጠ ይገኛል። የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ቁስ አካ ላዊ ሥርዓቶችን የሚያስተባብርና የሚስተናብር የሐዋርያት ሥር ዓተ ማኅበር አስተዳደር መሆኑን መገንዘብ የቤተ ክርስቲያን ባለቤ ትነት ቅድመ ሁኔታ ነው።

‹‹ጸጋ በዲበ ጸጋ ተውህበ ለነ›› በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ አስቀድሞ ሁሉ በእርሱ የሆነ ወደ ፊትም በአዳኝነቱ ሁሉ በእርሱ የሚሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ለብሶ ወደዚህ ዓለም ስለሚመጣ አስተማረ *‹‹ጸጋ በዲበ ጸጋ ተውህበ ለነ››* በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል አለ፤ (ዮሐ.1፥16)

አንዱ ጸጋ ኦሪት ነው፤ የኦሪቱ ሕግ ነው። ሌላው ጸጋ ወንጌል ሐዲስ ኪዳን ነው፤ የኦሪቱ ሕግ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማስፈጸም የተመሠረተ ነው፤ ይሁንና የሐዲስ ኪዳን ማለትም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ለምን አስፈለገ? የቀደመው የኦሪቱ ሕግ ስላልጠቀመና ወደፊትም የማይጠቅም ፈራጅ ገዳይ ስለሆነ ነው።

ሕግ ተፈጻሚነትን ቢያገኝ ኖሮ መልካም ነበር፤ ሌላ ጸጋ ባላስፈለገም ነበር፤ ነገር ግን ተፈጻሚነትን አላገኘምና አልጠቀመም፤ ስላልጠቀመም ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ የሚሻል ተስፋ ሐዲስ ኪዳን መጣ ተባለ (ዕብ 7፥18ና19)

ሆኖም ተስፋውን ለሚቀበሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ተሰጣቸው፤ የሕግ አለመጥቀም ደካማነት ተሻረ እንጂ ትእዛዙ አልተሻረምና የቀደመውን ሕግ ተክቶ የመጣውን የተስፋ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ስለ ተወለዱና በእግዚአብሔር ጸጋ ስለሚጠቀሙ ከሕግ ወቀሳና ፍርድ ነፃ ናቸው፤ ሕግ በእነርሱ ላይ የመፍረድ ሥልጣን የለውም፤ በሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ራሳቸውን ያስገዙ ናቸውና።

የእግዚአብሔር ምሕረት ሊጸና የቻለው ሰው ሕግን በመፈጸሙ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ የተጎበኘ ስለሆነ ነው። በዚህ

ጊዜ ነው በሕጋዊነት የማያስመካና ሕግን የሚያስፈጽም ጸጋ የተገ ኘው ‹‹ለኛ ፍጥረቱ ነንና ስንዚለብሔር ስለቀደሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በሲየሱስ ክርስቶስ ተፈጠርን›› እንደሚለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (ኤፌ. 2፥10)

ሰው ሥራን መሥራት የሚችለው ሕይወት ጤንነትን ሲያገኝ ነው፤ ሕይወትም በመንፈስ እንጂ በሥጋ ያለመኖር ነው፤ አሁ ንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በሲየሱስ ክርስቶስ ያለው የሕይ ወት መንፈስ ሕግ ከኃጢያትና ከሞት ሕግ ስርነት ስውጥቶኛል ስሕግ ያልተቻለውን ስንዚለብሔር የገዛ ልጁን በኃጢያተኛ ምሳሌ በኃጢያተኞ ምክንያት ልክ ስደር ገስደና›› እንዲል (ሮሜ.8፥3ና4)

የሥጋ ሕይወት ራሱን የቻለ የመንፈሳዊ ሕይወት ኃይል ፈቃ ደኝነት ካልተተካበት በመንፈስ የማይታደስ የዓለም ድካም እየበዛ በት መንፈሳዊ ሥራ አይከናወንለትም፤ ቤተ ክርስቲያን የዓለም በሽታ እየገባባት አካሏ (አንድነቷ) እየተለያየ ስትረበሽ ትኖራለች፤ ችግሯ ከውስጥ ነው ከውጭ አይደለም፤ የውስጥ ኃላ ቀርነትም ሀገርንና ወገንን ሲበድል ይኖራል። ቤተ ክርስቲያን በሥሪቷ በሥርዓተ ማኅ በር አስተዳደር የሥራ ድርሻዋን ካልተወጣች የሀገርን ኢኮኖሚ ትነ ካለች ማለት ነው፤ ምእመናን የሚቆሙት ለቤተ ክርስቲያን ዕድ ገት ነው፤ ምእመናን ሲቆሙላት በሥርዓቷ ጸንታ ካልቆመች ፈተና ላይ ስትወድቅ ትኖራለች፤ ከሕግ ፍርድ ማምለጥ አትችልም።

ቃላት ሲደጋገም ግልጽ ይሆናልና ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል ሲል ምን ማለት ነው? ዓለም ዳግም ተወልዶ ካልዳነ ሕግን መፈጸም አይችልምና የኋለኛው ጸጋ የቀድሞውን ጸጋ ሕግን እንዲያስፈጽም ተሰጠን ሲል ነው።

ዕውር ዕውርን ቢመራ ተያይዘው ጉድጓድ እንዳይወድቁ፤ ዓለም ዓለምን ሲመራ ጨልሞበት እንዳይጠፋ ብርሃን ወደ ዓለም እንደ

መጣ ዮሐንስ መሰከረ፤ በወቅቱ ተቃዋሚ ኃይሎች ቢኖሩም አልካ ደም መሰከረ ቃል ሥጋ እንደሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ እንደሚያድር ክብሩንም እንደምናይ እየገለጸ ከኋላው የሚመጣ ውን ጌታን ሰበከ።

ሥጋን ለብሶ ወደ ዓለም የመጣው ጌታችንም ‹‹ስነ ዮሃስም ብር ሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወተ ብርሃን ይሆንስታል፤ ስስነ የሚያምን ሁሉ በጨለማ ስንዳይኖር ስነ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ዓለምን ሳድን ስንጂ በዓለም ልፈርድ ስልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የም ፈርድበት ስነ ስይደሰሁም የሚመጣኝ ቃሌንም የማይቀበለው ስርሱ የሚፈረድ በት ሰለው፤ ስነ የተናገርኩት ቃል ስርሱ በመጨረሻ ቀን ይፈርድበታል›› እን ዳለው ብርሃን የመጣው ብርሃን ሳለ በብርሃን ለመመሳለስ ነው (ዮሐ. 12፥46-49)

ብርሃን ወደ ዓለም የመጣው በጸጋ ላይ ጸጋ የተሰጠው ጸጋን ብቻ ለመካብ አይደለም ለሥራ ነው፤ የቀደመው ሕግ አልተፈጸ መም፤ ካልተፈጸመም ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም፤ ይቀስፋል ይጨ ፈጭፋልና እንዳይቀስፍ ወደ ጨለማ ወደ ገሃነም እንዳይጥል የቀ ደመውን ሕግ ለመፈጸም ነው። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ጨለማው ዓለማዊው አስተዳደር ሳይወርሳት በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ብርሃን፤ ውስደ ብርሃን ሆና ሕዝቧን ወደ ብርሃን ስትመራ ነው ዕድገትና የኋለኛው ጸጋ የሚበዛላት።

ኃጢያት እስካለ ድረስ የቀደመው ሕግ ባይሻርም ከኃጢአትና ከበደል ፍርድ ይልቅ የኋለኛው ጸጋ እንዲበዛ አስፈለገ፤ ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ (ዮሐ1፥9)።

የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም

ምዕራፍ 14

ያለፉትን ዘመናት የሚተካ ታሪክ ነው፤ ሰው እንዳስቀመጡት ባይገኝም እንኳ ታሪክ በየጊዜው ከተወሳ ከቦታው አይጠፋም፤ ታሪክ መንፈሳዊ እንደመሆኑ መጠን ሌላው ቢክደውና ቢዋሽበ ትም ሌላው እውነት ስለሚመሰክርበት ሕያው ሆኖ ይኖራል።

መንፈሳዊ ታሪክ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር አስተዳ ደር ሥራ ባልኖረበት ሥልጣንና የግል ጥቅም በበዛበት ጊዜ አስ ታዋሽ የለውም፤ በታሪክ የተዛመደ ትውልድ አይኖረውም፤ የቤተ ክርስቲያን ዝክረ ታሪክ በሥራ ካልተወሳ በምትኩ ሌላ ዓለማዊ ቀውጢ እየተፈጠረበት ተረስቶ ይቀራል።

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ሰብስቦ መያዝ የቤተ ክርስቲያን ሥር ዓተ ማኅበር ግን ከሌላው ከትውልድ ጋር አያዛምድም፤ የቤተ ክር ስቲያን ታሪክ በዓለማዊ አስተዳደር ተሸፍኖ ያለ መንፈሳዊ ሥነ ምግ ባር ቢያዝ ፍሬ አይኖረውምና በተግባር መታየት አለበት። መንፈ ሳዊ ታሪክ በሥራ ከተያዘ ወደ ሕይወት መሸጋገሪያ ይሆናል።

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕ ረት አሁን የምትገኝበት ቦታ ጥንት ፈለገ አሸከላ ኪዳነ ምሕረት ይባል ነበር፤ በአልአሜዳ ዘመነ መንግሥት ተስአቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡና በአክሱም እንደተሰባሰቡ አባ ሊባኖስም መንነው ዓለምን ንቀው ከሮም ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ ከአባ ጳኩሚስ ሥርዓተ ምንኵስናን ተቀብለው በጾም በጸሎት ብዙ ትሩ ፋት እንደሠሩ ገድላቸው ይመሰክራል።

ጻድቁ በጊዜአቸው የደብረ ሊባኖስን ገዳም ከመገደማቸው በፊት አሁን ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ወደ ተባለበት ቦታ ወደ

ቀድሞ ፈለገ አሸከላ ኪዳነ ምሕረት ሲደርሱ ታቦቷ ተገልጻላቸው ከተሰወረችበት ቦታ አውጥተው ገዳም ብለው ገድመዋት ብዙ መነ ኮሳት ሲጸልዩባት ፀበል ከመቅደሱ ፈልቆ ሕሙማን ሲፈወሱበት እንደቆየና ይህች ተራዳኢት ታቦት ከዚያ በፊትም በዚሁ ቦታ ብዙ የታሪክ ዘመናትን እንዳሳለፈች ይነገራል፤ ይታመናል።

ታሪክ ከቦታው ይቀመጣልና ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ አባ ሊባኖስ ያለው የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ሙሉ ታሪክ በእናት ሀገር በክልል ትግራይ ጉንዳጉንደ ገዳም ተጽፎና ተደጉሶ ይገኛል ይላሉ ታሪክ ጸሐፊዎች፤ እውነት ነው።

ነቢዩ ዳዊት አስቀድሞ *‹‹ፈለገ ዘጸውሀዝ ያስተፈስህ ሀገረ ስግዚ ሰብሔር››* የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ፀበል ከመቅደሱ ይፈል ቃል፤ ሕዝብንም ይፈውሳል ሲል በትንቢት እንደተናገረው ፈለገ አሸከላ ኪዳነ ምሕረት በዚህ ስም ዘመኗም ብዙ ሕዝብ ስትፈውስ ቈይታለች።

አሁንም ነቢዩ ዳዊት *‹‹ጻድቀሰ ከመ በቀልተ ይፈረ ወይበዝህ ከመ ዝግባ ዘሊባናስ ትኩሳን ስሙንቱ ውስተ ቤተ ስግዚአብሔር››* ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፤ እንደ ሊባኖስ ዝግባም ይበዛል፤ ጻድቃን በቤተ እግዚአብሔር ለቤተ እግዚአብሔር የተተከሉ ናቸው እንዳለው አባ ሊባኖስ በደረሱበት ቦታ ዛፍ መትከል፤ ገዳም መገደም፤ አፀድ ማብ ዛት በኪዳነ ምሕረትና በራሳቸው ስም ፀበል ማፍለቅ ሕሙማንን መፈወስ በጸሎታቸው ዕድል ፈንታቸው ነው።

አፄ ዘያዕቆብ ወደዚሁ ገዳም መጥተው በፀበሉ ፈዋሽነት ጤና አግኝተው ለገዳሙ የመተዳደሪያና የንዋየ ቅድሳት ስጦታ ማድረ ጋቸው ጉልቶ ይነገራል። ከዚህ ቀጥሎ ያለውም የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ታሪክ አሁን በአምነትና በረድኤት እንደምናየው ነው።



የምሕረት ቃል ኪዳን

ከአዳም እስከ ኖኅ ከኖኅ እስከ አብርሃም ያለው ሃያ ትውልድ የቃል ኪዳን ዘሩን እንደያዘ ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ ቃል ኪዳን ጋር ተገናኘ፣ እሥራኤል የእግዚአብሔር የሕጉን ጽላት ተረካቢ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆነ፤ ያዕቆብ ከመሬት እስከ ሰማይ የሚደርስ መሰላል በራዕይ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በአጠገቡ ቆሞ በአንተና በዘርህ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ሲል በቃል ኪዳኑ የያዕቆብን ትውልድ ባርኳል፤ (ዘፍ. ፲፪÷፭፡፪ ም.ጽ፰÷፲-፲፪)

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እቴጌ ጣይቱ ብጡል ካህናትን ይዘው ፈለገ አሸክላ ኪዳን ምሕረትን በኖኅ ቃል ኪዳን ስም ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ብለው በማኅበር ገዳም ስም ሰይመ ዋታል፤ ሐመረ ኖኅ ተብላ የተሰየመችበት ምክንያትም የኖኅ መር ከብ ኖኅ በውስጧ ሆኖ ከውሃ ጥፋት እንደዳነባት በዳግም ልደት በዓመተ ምሕረትም ምሳሌ ድንግልና ምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሆነች ነው።

አሁን በእምነት ወደ ሚታየው ወደ ታቦታ ተራዳኢነት ስናተ ኩር የታቦታ ተራዳኢነት እየበዛ መጥቷል፤ ከፀበሉ ፈዋሽነት የተ ነሣ ምእመናን ትሩፋት እየፈጸሙባት ይገኛሉ፤ ከሃያ አምስት ዓመት በፊት አቶ አስፋው ገብረ ሕይወት የተባሉ ወርቅ ነጋዴ ለሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ሰፊ የኤሌክትሪክ መሥመር አዘር ግተው መብራት በማስገባታቸው ትሩፋታቸው በታሪክ ውስጥ የሚ ታወስ ነው፤ በአጠቃላይ ለሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት የቆሙም ምእመናን ትሩፋታቸው ሰፊ ነው።

የአዲስ አበባና የክፍላተ ሀገር ምእመናን ከሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት መቅደስ ከሚፈልቀው ፀበል እየተጠመቁ እንደመዳናቸው መጠን ጥዋትና ማታ ከአፀደ ቤተ ክርስቲያኗ አይለዩም፤ ወደ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ፀበል በየቀኑ የሚጎርፈው ሕዝብ ብዛት አንጻር የከተማ አውቶቡስ ስለተመደበ ወደ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ለማምራት የትራንስፖርት ችግር የለም።

ቤተ ክርስቲያን ይህን ያህል ምእመናን ሲቆሙላት አለቆቿ አልቆሙላትም፤ በሥሪታ በሥርዓተ ማኅበር አልጸናችም። አለቆቿ ሠርከ ኅብስታን ይዘው ወደ ውጭ ዓለም እየወጡ ቤተ ክር ስቲያን ለእነርሱ የምታካብተውን ክብር ወደ ዓለማዊነት ሐሳር እየተለወጠ ነው።

ሥልጣን እርስ በርሱ አይስማማም፤ በሥልጣን እየተፋጀ ይለ ያያል፤ ማኅበራዊ ሥርዓት ግን አንድ ቃል አንድ ልብ አለው፤ የሥራ ዕድገቱም የተመሰገነ ነው፤ ስለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን ማኅበር ተብላ ማኅበር ሆና የተመሠረተችው።

የሥልጣን ውዳሴ ከንቱ የአካልና የታሪክን ዕድሜ አይቀጥ ልም፤ በእግዚአብሔር ቃል የሚኖር ግን እንደ አቡነ ሊባኖስ በወ ንዝ ዳር እንደተተከለ ፍሬውን በየጊዜው እንደሚሰጥ ቅጠሉም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል (መዝ.1፡3)።

ክፍል ሁለት

በመሠረቱ መነኮሴ ቢያገኝም በሥርዓተ ማኅበር ቢያጣም ለማግኘት በሥርዓተ ማኅበር ሲኖር እንጂ ሲያጣም ወደ ዓለም ሲያገኝም ወደ ዓለም የሚጓዝ ከሆነ ጉዞው ‹‹ሕማም ዘዘቧፍ›› የዘወ ትር በሽታ ሆኖ ፍጻሜው ሐሳርና ሞት ነው። ይህም የሚሆነው ከገዳማት እየተመረጡ የሚሾሙት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በተ ሚላ ሠርከ ኅብስትና በተሚላ የቤተ ክርስቲያን መኖሪያ ቤት ያለ ደመወዝ በባለቤትነት ተወስነውና ገዳማትን መከታ አድርገው ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሥሪቷ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ስለ ማይመሩ ነው።

እግዚአብሔር በበጎ ፈቃዱ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ተለይታ በሕይወት የምትኖርበትን ሕግንና ሥርዓትን ገድቦላታል፤ የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ቀኖና የሐዋርያት ሥርዓት ማኅበር አስ ተዳደር ነው። ሕግና ሥርዓት ማለት ገደብ ማለት ነው፤ በቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ሥርዓት ያልተጠበቀ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና የግል ትሩፋት ብቻ እየሆነና ወደ ዓለም እየተለወጠ ሊቀር ይችላል። በቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ማኅበርን አስተዳደር ገደብ ማለፍ ቀኖናን ማፍረስ ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከዓለማዊነት የተለየ ባሕርይ ነው ያላት፤ ሥል ጣን ወይም ለሥልጣን መገዛት ከሞተ ሥጋና ከሞት ነፍስ አያድ ንም፤ ፍቅር ወይም ሥርዓተ ማኅበር ግን ሁሉን ይሸፍናል፤ ከሞተ ሥጋና ከሞት ነፍስ ያድናል፤ በሥልጣንና በግል ጥቅማ ጥቅም የምትለያይ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ቢኖራት እንኳ ሀብታም፤ ባለጸ ጋም፤ መጠጊያም መሆን አትችልም፤ ቀኖናዋም ያልተጠበቀ ይሆንባታል።

የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በባለቤትነት ከተሰጠቻቸው ቦታ ከቤ ታቸው ከቤተ ክርስቲያን ደመወዝ እየተቀበሉ የቤተ ክርስቲያንን ሠርከ ኅብስት በደመወዝ ስም ወደ ውጭ ዓለም የሚያወጡና ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር የማያስተዳድሩ ከሆነ ገዳማትም አስተዳደራቸውን ማኅበራዊ ሠርከ ኅብስታቸውን ወደ ዓለማዊነት መለወጥ ግዴታ ይሆንባቸዋል ማለት ነው።

የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ውስጥ ዙሪያ ጠባብ ነው። እንደ ሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ከሆነ ከዓውደ ምሕረቱ አጥር ውጭ ብዙ የሚሠሩ ሥራዎች አሉ።

ምናልባት ገዳማት የወደፊት ቀኖናቸው ይጠበቅ፣ እንደሥሪ ታቸው በማኅበር ይተዳደሩ ከተባለ ወሳኙ ማን ነው? ከገዳማት የሚወለዱ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ያለ ደመወዝ በባለቤትነት ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ኃላፊነት ነው።

የቤተ ክርስቲያን ባለቤት መሆን የውዴታ ግዴታ ነው፤ ትር ጉሙም የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ማለት ነው፤ አንድነት ሊከ ናወኑ የሚችሉ ብዙ የሥራ ዘርፎች ይኖሩታል፤ መቼም ቢሆን በፈቃደኝነት ያልተደገፈ ያለ ውዴታ በግዴታ የሚከናወን መን ፈሳዊ ጉዳይ አይኖርም።

የተሟላ ሠርክ ጎብስትና የተሟላ የቤተ ክርስቲያን መኖሪያ ቤት እያለ የቤተ ክርስቲያን ባለቤትነት አደራነትን ከተረከቡ በኋላ በደመወዝ ስም የዓለም ጎጆ ወጪ መሆን ትርጉሙ ዓለማዊነት ነው፤ ዓለምም ሞት እንጂ ሕይወት አይገኝባትም።

ዓለም ያጐድላት እንጂ አያተርፍም፤ ለአብነት ያህል ከሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም እግርጌ ከፀበሉ መጠመቂያ አካባቢ ቤተ ክህነት ከመንግሥት የተረከባቸው ጥንት የተሠሩ ያረጁ ያፈጁ ፍትሕ መንፈሳዊ የማይታይባቸው በቁጥር 23 የሚያህሉ የጭቃ ቤቶች ይገኛሉ፤ በግብረ ጠልነት ተወርሰው የነበሩ ይመስላል።

በአሁኑ ጊዜ በውስጣቸው የሚኖር ሕዝብ በግድግዳው የጭቃ ልስን ላይ ጭቃን እየለጠፈ ከላይ ሽራ እያለበሰ ይኖርባቸዋል፤ በደርግ ዘመን እንደተተመነለት ብር 3.4 ኪራይ ለቤተ ክህነት ይከፈላል፤ ቢከፈልም በቤተ ክህነት ባለቤትነት አይተማመንም፤ ቤቶቹም ሁነኛ ባለቤት ያላቸው አይመስሉም።

ይሁን ተብሎ በጥናት ያልተሠሩ ከኑዛዜ የተገኙ ቢሆንም ኑዛዜ ለሁነኛ የቤተ ክርስቲያን ባለቤት እንጂ ለምንደኛ ዓለማዊ ስንፍና አያወርስም። የሚኖርባቸው ሕዝብ በየቀኑ ብር 4ና 5 ኪራይ እየከፈለ ፀበል የሚጠመቀውን ሕዝብ እየተጠባበቀ የሚ ተዳደርባቸው እንጂ አቅም አግኝቶ ቤቶቹን ነፍስ የሚዘራባቸው አይደለም። ቤቱን እየለቀቀ የሚያከራይም አለ፤ በአሁኑ ጊዜ ከነ ዚህ ቤቶች የተለቀቀ ቤት ሲገኝ ቤተ ክህነት በአዲስ ተመን አንዱን ጠባብ አሮጌ ክፍል በብር 60 ያከራያል፤ እንደ አካባቢውና ርቀቱ መጠን ፍትሕ መንፈሳዊ የለውም፤ ከሙስና የተረፈ ዓለም ያው ሙስና ነው።

ይጠቅማሉ ተብሎ ከምእመናን ለቤተ ክርስቲያን በውርስ የተሰጡ ቤቶች ሠርቶ በመብላት ረገድ አካላቸው በሙሉ ታድሶ በነፃና በተመጣጣኝ ዋጋ ማለትም ቢበዛ በብር 30 - 40 እየተ ከራዩ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር የሕዝብ መገልገያና የገዳሙ ግርማ ሞገስ የሚሆን የጽድቅ ሥራ ሊሠራባቸው ሲገባ የጉልት ገበያ ሁነው ይገኛሉ፤ ይኸውም ሳይሠሩ መብላት ማለት ነው።

ችግሩ የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት በዝባዥ የሥራ ውጤት ነው፤ የቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድ ሆኖ በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር እስካልተዋቀረ ድረስ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የገዳማትን ሕይወት አይጠብቅም። ይሁን እንጂ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ደመወዝ ሳይበሉ ባለቤቶች ከሆኑ ምንደኞች የቤተ ክህነት ባለ ሥልጣኖችንም በሥርዓት ሊያሠሯቸው ይችላሉ፤ አብረውም የሞት ዓለምን ይገታሉ።

የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ለመናንያን ማኅበራዊ ሥር ዓት የተመቸ ወደ ገነት የሚያደርስ መርኅ እንደ መሆኑ መጠን ሠርክ ጎብስትን የሚያበዙ መንፈሳዊ ሥራዎች የሚከናወኑበት ቦታ ነው።

የቤተ ክርስቲያን መለኪያ ዕውቀትና ስነ ምግባር ነው፤ ዕው ቀትም የሞት ጥቅሙን ሲጠቀም እንደሚኖር የዓለም ዕውቀት አይደለም፤ በሚበጀው በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመረተ አእምሮ ነው፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን የተወ ገና ከዚህ ዓለም ሳያልፍ በሕይወት ሳለ ‹‹ጠቶ ስጥፍ ዋጋን ያገኛል፤› ‹‹የሚጠጣ ውም ዓለም ጠንግሥተ ሰማያትን ይቀበላል›› ይላል (ማር.10÷29 እና 30)።

‹‹ምዕተ ምክብዒተ ህየንተ ዓለም›› ዓለምን ለተወ በዓለም ፈንታ መቶ ዕጥፍ ዋጋን ማግኘት የሚቻለው በመንፈሳዊ ሥራ ነው፤ ልብን በሁለት ዓለም ሳይከፍሉ አንድ ወጥ የቤተ ክርስ ቲያን ባለቤት በመሆንና የቤተ ክርስቲያንን ሠርክ ጎብስት በደ መወዝ ስም ወደ ውጭ ዓለም ሳያወጡ ቤተ ክርስቲያንን በሥር ዓተ ማኅበር አስተዳደር የመምራት መልካም ዕድል ሲኖር ነው።

የቤተ ክርስቲያን ባለቤትነት ያለ ደመወዝ በሥርዓተ ማኅበር የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ኃላፊነትና ተግባር ሲሆንና በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ኖላዊነት ጠባቂነት ለደመወዝ ሞያተኛው ሠራተኛ የተሻሻለ ደመወዝ እየተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ሥራ በአንድነት ሲከናወን ‹‹ምዕተ ምክብዒተ›› ዓለም የማያደናቅፈው የመቶ ዕጥፍ ዋጋ ያለው ክብር ይገኛል ማለት ነው።

ዓለምና ቤተ ክርስቲያን በምግባር አይስማሙም፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሰላምን ለመስጠት የመጣሁ አይ ምሰላችሁ ሰይፍን መለያየትን እንጂ ያለው የሚያምን ከማያምን ጋር መኖር አይመቸውምና ማለት ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር አንድ ከሆነች ሰላም አታገኝምና ከዓለማዊ ተግባር የምትለይበትን የመንፈስን ሰይፍ ለማስታጠቅ ነው (ሉቃ.12፥51) ዓለም የማ ይሞላለት የሞት ነጋዴ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ግን የመቶ እጥፍ ዋጋ አትራፊ እንድትሆን ነው የተመሠረተችው።

ሲኖዶስ የገዳማት አካል ነው

ዓለም አይቃናም፤ ቢያጥቡት ያድፋል እጅ፣ ቢመክሩት ያጠፋል ልጅ እንደሚባለው ዓለም ካለፉት የጥፋት ዘመናት አይማርም፣ እንዲ ያውም ይብስበታል፣ ዓለም ካልሸሹት ሚና ካልለዩበት በቀር አይቃ ናም። ዓለም የሞት ማኅደር ነው፤ የሕይወት አይደለም፣ ዓለማዊ ሥል ጣንም ብሽታ ነው ሕይወት አይደለም፤ የጋራ ሕይወት የቤተ ክርስቲያን አንድነት ነው፤ ሕይወትም በእምነትና በተግባር ሲንከባከቡት ይበዛል።

በዚህ ዓለም ራሱን ሊጠቅም እንጂ ራሱን ሊበድል የሚፈልግ የለ ምና ሕይወትን መልበስ የሚቻለው ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን ሲቆሙ ቤተ ክርስቲያን ከሞት ዓለም ነፃ ታወጣቸዋለች፤ ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገሪያ ትሆናቸዋለች ድምጿ ሁል ጊዜ እረኛቸው ይሆናል።

ይሁን እንጂ ማኅበራዊ ሚና ያልተለየባት ቤተ ክርስቲያን ወደ ዓለ ማዊነት እየተለወጠች ኑሮዋ የሞት ዓለማዊነት እየሆነ በስም ብቻ ትኖ ራለች እንጂ ሕልውናዋ የመንግሥተ እግዚአብሔርን ርስት አያበዛም የሞት ዓለም ይሰፍንባታል።

የቤተ ክርስቲያንን ምንነት ከተገነዘብንና ቤተ ክርስቲያንን እንደ ግል ሕይወታችን ከቆጠርን ሁለመናችንን ለእግዚአብሔር አስተዋጽኦ ልናደርግ እንችላለን፤ ሆሞ ቤተ ክርስቲያን ምን ማለት ናት? አቀማ መጧ እንዴት ነው?

ቤተ ክርስቲያን በቃለ እግዚአብሔር መሣሪያዋና ትጥቋ ማኅበር አንድነት ማለት ናት፤ አለቀቿ ማኅበር ናቸው፤ ዓለም ወይም ሥልጣን የማይበታትናቸው ናቸው፤ ዓለምን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚ ያስገዙ እንጂ ዓለም የሚገዛቸው ማለት አይደሉም፤ ለዓለም አልተሠ ሩም ዓለማዊውንና መንፈሳዊውን ለይቶ የሚያስቀምጥ የቤተ ክርስ ቲያን ገንዘብ አያያዝ ነው፤ በየትም የዓለም አህጉር የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የማኅበር ነው፤ የዓለም አይደለም።

ቤተ ክርስቲያን ዋስትና ያላት የሰማዩም የምድሩም ሀብተ ጸጋ በእጇ ነው፤ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ገንዘብ ካልሰበሰብኩ ሳሪጅ ማን ይጠረኛል? ስሞት ማን ይቀብረኛል? አይሉባትም፤ የቤተ ክርስቲያንን የገንዘብ አያያዝ ዓለማዊ ሲያደርጉት ለመለያየት ይሆናል፤ መንፈሳዊ ሲያደርጉት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መገንቢያ ይሆናል። አንድነት የቤተ ክርስቲያን አጥር ነውና በገንዘብ ፍቅር ከቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ የቤተ ክርስቲያኗ ድርጅት ነኝ የሚለውን አያስተናግድም።

ቅዱስ ሲኖዶስ የገዳማት አካል ነው፣ አንድ አካል ሁለት አይሆ ንም፤ አንዱ ግንድ ብዙ የበረከት ቅርንጫፎች ሲኖሩት ይችላል፣ የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት የሲኖዶስ ጋሻ መከ ታዎች ናቸው። ሲኖዶስ ከገዳማት ተለይቶ በከተማ ቀልጦ የሚቀር ማለት አይደለም፤ ከገዳማት ሥርዓት የተለየ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሥር የለውም።

ቅዱሳት መጻሕፍትና ቀኖናዎች ከገዳማት የተገኙ ናቸው፤ መንፈሳዊ ሥርዓት ሁሉ ከገዳማት ነው፤ ‹‹ከጽዮን ሕግ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና›› (ሚክ.4:2ና3) የመንበረ ፓትርያርክ ሠርከ ጎብስት ከገዳማት ሠርከ ጎብስት ጋር ቢቀላቅሉት ይበዛል ይዳብራል እንጂ አያንስም::

የሲኖዶስ ጉባኤና ቀኖና ገዳማት ናቸው፤ ሲኖዶስ የገዳማት ጉባኤ ማለት ነው፤ ገዳማት የቅዱስ ሲኖዶስ መመሪያዎች እንደመሆናቸው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ከገዳማት ተወልደውና ተመርጠው ለሹመት ሲመጡ ገዳማትም አብረው መምጣት አለባቸው:: የገዳማት መንፈሳዊ ኃይል ሲቀር ዓለም ለቤተ ክርስቲያን አንድነትና ተግባር ምክንያት ሊሆን አይችልምና ገዳማት ለቤተ ክርስቲያን አንድነት አብነት ይሁኑ፤ ከመነኮሱ በኋላ ከገዳማት ጥላ ሥር ተለይቶ መኖር ዓለማዊነት ነው፤ ዓለማዊነትም ቤተ ክርስቲያንን የውጭ ርዝራዥ ያደርጋታል እንጂ ስለ ማኅበራዊ ኑሮና ሕይወት ድጋፍ አይሆናትም::

የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አባቶች ደመወዝ መብላት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ያፈርሳል፤ ጭቁኑን ሠራተኛ ያሰበቂ ደመወዝ ማሠራትም ቤተ ክርስቲያን ይበድላል፤ ቤተ ክርስቲያን በአሠሪ ባለቤትና በደመወዝ ሞያተኛ የተጣጣመ አንድነት ነው ያላት::

ሆኖም መንበረ ፓትርያርክና የሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና በጥበብ የታነጹና በተሟላ የቤተ ክርስቲያን ሠርከ ጎብስት የተገነቡ ገዳማት መሆን አለባቸው፤ አንድነት የሥነ ምግባር ኃይል ነውና በተመቻቸ ማኅበራዊ ኑሮ የተመቻቸ የቤተ ክርስቲያን ሥራ መሥራት ወንጌልን ማስተማርና ልማትን መዘርጋት ይቻላል:: በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከአንድ እስከ መጨረሻ ሰማይ ጠቀስ ዕድገት ይኖራታል::

የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ያለ ደመወዝ በተሟላ ሠርክ ጎብስት ተወስነው የቤተ ክርስቲያን ባለቤቶች እንዲሆኑ የተገባቸው ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት ለማስቀመጥና ለመንፈሳዊ ትውልድ ለማስተላለፍ፤ ክብራቸውንና ኃላፊነታቸውን ለማስጠበቅ ነው::

ከ፪ሺ፩ - ፪ሺ፲

፪ሺ፩ ወንጌላዊው ማቴዎስ ዘ.መ ማክሰኞ አበቅቴ ፲፰ መጥቅዕ ፲፪ የዕ.ተውሳክ ፮ ጾ.ነነዌ የካ ፲፰ ዐ.ጾም መጋ ፪ ደ.ዘይት መጋ ፳፱ ሆሣዕና ሚያ ፳ ስቅለት ሚያ ፳፭ ትንሣኤ ሚያ ፳፯ ር.ካ ግን ፳፩ ዕርገት ሰኔ ፮ ጰራቅሊጦስ ሰኔ ፲፮ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፲፱


፪ሺ፪ ወንጌላዊው ማርቆስ ዘ.መ ረቡዕ አበቅቴ አልቦ መጥቅዕ አልቦ የዕ.ተውሳክ ፫ ጾ.ነነዌ የካ ፫ ዐ.ጾም የካ ፲፯ ደ.ዘይት መጋ ፲፱ ሆሣዕና ሚያ ፭ ስቅለት ሚያ ፯ ትንሣኤ ሚያ ፲፪ ር.ካ ግን ፮ ዕርገት ግን ፳፩ ጰራቅሊጦስ ሰኔ ፩ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፬

፪ሺ፫ ወንጌላዊው ሉቃስ ዘ.መ ሐሙስ አበቅቴ ፲፩ መጥቅዕ ፲፱ የዕ.ተውሳክ ፯ ጾ.ነነዌ ጥር ፳፭ ዐ.ጾም የካ ፱ ደ.ዘይት መጋ ፯ ሆሣዕና መጋ ፳፯ ስቅለት ሚያ ፪ ትንሣኤ ሚያ ፭ ር.ካ ሚያ ፳፰ ዕርገት ግን ፲፫ ጰራቅሊጦስ ግን ፳፫ ጾ.ድኅነት ግን ፳፯

፪ሺ፬ ወንጌላዊው ዮሐንስ ዘ.መ ቅዳሜ አበቅቴ ፳፪ መጥቅዕ ፭ የዕ.ተውሳክ ፯ ጾ.ነነዌ የካ ፲፬ ዐ.ጾም የካ ፳፰ ደ.ዘይት መጋ ፳፭ ሆሣዕና ሚያ ፲፯ ስቅለት ሚያ ፳፩ ትንሣኤ ሚያ ፳፫ ር.ካ ግን ፲፯ ዕርገት ሰኔ ፪ ጰራቅሊጦስ ሰኔ ፲፪ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፲፭

፪ሺ፭ ወንጌላዊው ማቴዎስ ዘ.መ እሑድ አበቅቴ ፫ መጥቅዕ ፳፯ የዕ.ተውሳክ ፪ ጾ.ነነዌ ጥር ፳፱ ዐ.ጾም የካ ፲፫ ደ.ዘይት መጋ ፲ ሆሣዕና ሚያ ፩ ስቅለት ሚያ ፮ ትንሣኤ ሚያ ፱ ር.ካ ግን ፪ ዕርገት ግን ፲፯ ጰራቅሊጦስ ግን ፳፯ ጾ.ድኅነት ግን ፴

፪ሺ፮ ወንጌላዊው ማርቆስ ዘ.መ ሰኞ አበቅቴ ፲፱ መጥቅዕ ፳፮ የዕ.ተውሳክ ፭ ጾ.ነነዌ ጥር ፳፩ ዐ.ጾም የካ ፭ ደ.ዘይት መጋ ፰ ሆሣዕና መጋ ፳፫ ስቅለት መጋ ፳፰ ትንሣኤ መጋ ፴ ር.ካት ግን ፳፱ ዕርገት ሰኔ ፱ ጰራቅሊጦስ ሰኔ ፲፱ ጾ.ድኅነት ሰኔ ፳፪



ከዚህ በፊት ያዘጋጀኋቸው መጻሕፍት

- የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር
- የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር 2ኛ
- ቤተ ክርስቲያን ከሕግ በላይ ናት
- የቤተ ክርስቲያን መጋቢ
- ከሕግ በላይ እንዲሆኑ
- መናፍቃንና ግብራቸው
- የቤተ ክርስቲያን ሠርክ ጎብስት

ወደፊት የማዘጋጃቸው

- ሠርክ ጎብስት ተከታይ
- ሕጋዊ የቀበሮ ባሕታዊ
- አሮጌውን ተውት አዲሱን ልበሱት